# የካህናት ተልእኮ፤

በሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ

፱፻

www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም ፤

ይህ የካህን ተልእኮ በማለት የቀረበው ጽሑፍ ካህኑ ሊያደርገውና ሊፈጽመው የሚገባው ምንና ምን እንደሆነ ለይቶ የሚያስረዳ ነው ።

ካህን ማለት የበቃ፤የነቃ፤ከሁሉም ነገር የተለየ፤ለእግዚአብሔር አገልግሎት ብቻ የተሠለፈ ማለት ነው ፤ ስለዚህ ካህን ከተሾመበት ማለት ካህን ከሆነበት ዕለት ጀምሮ ከሰው ተራ ወጥቶ በሰማያዊ ነገድነት የተመዘገበ ምድራዊ መልአክ ነው ። ካህን ከምድራዊ ንዝንዝና ጭቅጭቅ የራቀ፥ማዕርጉን የጠበቀ፥በዕውቀት ግን የላቀ ክፉውንና ደጉን የለየ፤ምንን መሥራት ምንን መተው እንዳለበት ዐውቆ የሚኖር ነው ። ካህን የሚሆን ሁሉ በሕይወቱ ፥ በልብሱ ከሌላው ሰው ሁሉ ተለይቶ የሚታወቅ መሆን አለበት ። ካህኑ ራሱን ያወቀ ራሱንም የጠበቀ ስለሆነ ሁሉ ያከብረዋል፥ እንደ እግዚአብሔር መልአክም አድርጎ ይቀበለዋል፤ የሚናገረውን ይሰማል፤ በዚህ መልክ እርሱም ተልእኮውን እንደ ዓላማው ይፈጽማል ። ካህን በዘሩ በወገኑ ግዴታ ኑሮበት የሚሾም አይደለም ፤ እንዲሁም እንደ ግብር ዕዳውን ለመወጣት ብቻ የሚሾሙ አይደለም ፤ የሚቀበለው ሥልጣን ሰው ሠራሽ ሳይሆን እግዚአብሔር የፈቀደው ነው ፤ ስለዚህ እርሱን በትክክል ለማገልገል ፥ ሕዝበ እግዚአብሔር የሆነውንም ምእመን ለማስተማር ቆርጦ የተነሣ መሆን አለበት ። ለእግዚአብሔር አምልኮት ለማቅረብ ቆርጦ ካህኑ ሲነሣ እግዚአብሔርም ሲፈቅድለት ምእመናንም ሲመርጡት የተሾመ እንደሆነ እንደ ዓላማው ይፈጽማል ።

ቅዱሳን ሐዋርያት በዚህ መልክ መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ መረጣቸው ፤ ሀብተ ክህነትንም ፥ ሥልጣነ ክህነትንም ሰጣቸው ፤ የክህነትን ተልእኮ እንዲፈጽሙ ሥልጣኑን ሰጥቶ ወደ ዓለም አሠማራቸው ።

የሐዋርያት ተከታዮች የሆኑ ሁሉ በሐዋርያት መራጭነት ፥ በእግዚአብሔርም ጠሪነት በአንብሮተ እድ ተሾሙ ፥ ካህን ሊቀ ካህናት ሆኑ ፤

የሐዋርያት ተከታዮች የሆኑ ሁሉ በሐዋርያት መራጭነት ፥ በእግዚአብሔርም ጠሪነት በአንብሮተ እድ ተሾሙ ፥ ካህን ሊቀ ካህናት ሆኑ ፤ በተሾሙበትም ቦታ ፥ በተሾሙበትም ዓላማ ሠሩ፥ ስለዚህ ተልእኳቸውን በሚገባ ፈጸሙ ።

አሁንም በጊዜያችን የሚነሡ ካህናት የሐዋርያት ተከታዮች ሆነው የሚሠሩ ፥ በእነርሱ እግር በትክክል የተተኩና የሚተኩ መሆናቸውን አምነው የሚሠሩ መሆን አለባቸው ።



www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ይኸችም ትንሽ ጽሑፍ የምታስገነዝበው እንደመረሳት እያለ የሄደው የካህኑ ተልእኮ ምንና ምን መሆን እንደሚገባው ነው ። ምንም ሥጋዊ ሹመትም ቢሆን ለሥራ መሾሙ የታወቀ ቢሆንም የካህኑ ሹመት ግን ዕጥፍና ድርብ የሆነ ኃላፊነት ያለበት ፤ ከባድ ሥራም የሚሠራ መሆኑን ዐውቆ እያንዳንዱ ካህን እንደ ዓላማው ለመፈጸም ይችል ዘንድ መብቱንም ግዳጁንም የምትገልጥ ናት ።

ካህን የሆነ ሁሉ ይኸችን ጽሑፍ በማንበብና በማጥናት ራሱን እንዲያስተካክል በእውነተኛውም የካህን ጐዳና እንዲራመድ ትመራዋለች ።

ካህን ለመሆን ገና የሚመኝ ፤ በዚህም ዓላማ የሚሠለጥን እንዳለ ደግሞ የኃላፊነቱን ከባድነት ፤ የሥራውን ብዛት አይቶ ይሁንብኝ ብሎ እንዲገባና ተልእኮውን በሚገባ ለመፈጸም ብቁ ሆኖ እንዲገኝ የምታደርግ ጽሑፍ ናት ።

ካህኑ ማዕርጉ ምጡቅ ፤ አእምሮው ረቂቅ ሆኖ በትንሹና በዝቅተኛው ነገር ሁሉ የማይጨቃጨቅ ፤ እውነተኛውን የካህኑን ዓላማ ብቻ የሚመለከት ሆኖ ይገኝ ዘንድ ቤተ ክርስቲያናችን ይኸን መመሪያ ሰጥታለች።

ለራሱ ተልእኮውን ዓላማውን የሚያውቅ ፤ መንጋውን የሚጠብቅ መሆን አለበት ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ለተከታዮቹ ማስጠንቀቂያ መመሪያ ሲሰጥ የተናገራቸው ቃላት «አሁንም ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ለመንጋውም ሁሉ ፤ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ ጠባቆች አድርጎ የሾማችሁ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ እርሱ በደሙ የዋጃትን» የሚል ነበር ፤ (የሐዋ ፡ ሥራ ፡ ፳ ፡ ፳፰) ።

ካህናት ነን ብለን በካህን ስም ከቀረብን የሚጠብቀን ኃላፊነት ይኸን የመሰለ ነው ፤ ታዲያ እኛም ተልእኳችንን ዐውቀን ይኸን ለመፈጸም ዝግጁ ሆነን እንቅረብ ።

ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ



# ክፍል ፩ እውነተኛ ካህን

## ፩፡ የክህነት ትርጉም

ካህን ማለት ኮኼን ከሚለው ከዕብራይስጡ የተወሰደ ቃል ነው ፤ ትርጉሙም የተለየ ፤ የተቀደሰ ፤ ለእግዚአብሔርም አገልጋይነት ብቁ የሆነ ማለት ነው ፤ በእርግጥም እንደሚያመለክተው አንድ ሰው ካህን ሲሆን ልዩ ጸሎት ደርሶለት ፤ ልዩ ቡራኬም ተሰጥቶ በመንፈስ ተቀብቶ ነው ።

የብሉይ ኪዳን ካህን የብሉይም ሊቀ ካህን ይሾም የነበረው እግዚአብሔር በሚወደውና በሚፈቅደው መሥመር የተሠማሩና ለዚሁ አገልግሎት ብቁ ናቸው ተብለው ከተመረጡ ነገዶች ከነገደ አሮንና ከነገደ ሌዊ ውስጥ ነበር ።

እነዚህም ካህናት ከተለዩ ነገዶች ወጥተው ቢሰየሙም ገና ለሹመት በቀረቡ ጊዜ የተለየ ጸሎት የተለየም ቅብዓት ተሰጥቷቸው ይሰየሙ ነበር።

በብሉይ ዘመን የካህናት ምርጫና ሹመት በዚህ መልክ ሲፈጸም ይገኝ እንጂ ይኸ ሁሉ ለሐዲስ ኪዳን ካህን አምሳል መርገፍ በመሆን እንደተፈጸመ የታወቀ ነው ።

የሐዲስ ኪዳን ክህነት ግን ጀማሪ የሆነው እውነተኛው ካህን ሊቀ ካህን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። እርሱም ክህነቱ ዘለዓለማዊ ነው ፤ እንደመልከ ጼዴቅም ክህነት ነው።ሹመቱም ከዘር የወረደ ሳይሆን ከባሕርዩ የተገኘ ነው ፤ እንደ ትርጕሙ እውነተኛ ካህን ሆኖ የተገኘ ፤ እንደ ሊቀ ካህንነቱም ተልእኮውን የፈጸመ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፤ ምክንያቱም ካህን የሚሆን ስለ ሕዝቡ ኃጢአት መሥዋዕት የሚያቀርብ ፤ ጸሎት የሚጸልይ ፤ ሕዝቡን በትክክል ወደ ደኅንነት ጐዳና የሚመራ፤የእግዚአብሔር እውነተኛ አገልጋይ ፤ የተለየ የተቀደሰ ነውና ። ጌታችን ኢየሱስም ለዚህ ሁሉ እውነተኛ ምሳሌነቱን የሰጠ እውነተኛ ሊቀ ካህናት ነውና። ከዚያ በኋላ የሚነሣው ካህን ሁሉ እርሱን አብነት አድርጎ እውነተኛ ካህን ሆኖ በመገኘት እንዲሠራ እንጂ በስም ብቻ ወይም የካህን ልብስ በመልበስ ብቻ ካህን ነኝ እንዳይል ፤ ካህንም መስሎ እንዳይቀርብ ካህን የሚለው የስም ትርጓሜ ያስረዳል ። የሐዲስ ኪዳን ክህነት ጀማሪ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስም ምሳሌነቱን በሥራ ገልጦ አስረድቷልና ።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## ፫/ የክህነት አጀማመር ፤

የክህነት አነሣስ ከሰው ልጅ ድኅነት ፣ ከሰው ልጅም ማኅበራዊ ኑሮ ፍላጎት የተነሣ አምላክ የፈቀደው ማዕርግ ነው ።

ካህን የሚለው ስምና የካህን ተልእኮ ገና ሳይታወቅ የቤተሰብእ አስተዳዳሪዎች አባቶች እንደ ካህን ሆነው በካህንም እግር ገብተው ይሠሩ ፣ የካህኑን ቦታ ይዘው ተልእኳቸውን ይፈጽሙ ነበር ።

ከነዚህም አባቶች መካከል ጥቂቶቹ ፓትርያርክ (አርእስተ አበው) እየ ተባሉ የሚጠሩ ፤ የእግዚአብሔርንፈቃድ በትክክል የሚፈጽሙ ፤ እርም ጃቸውን በማስተካከል የእግዚአብሔርን ፍለጋ በመከተል የሠሩ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ምክር ፣ ተግሣጽ ለቤተ ሰብእ ሲሰጡ ፣ በመልካም ግብረ ገብነት ሲመሩ፣ ጸሎት ሲጸልዩ ፣ መሥዋዕት ሲሠው የኖሩ ናቸው ።

### ስም በመጥራት ጥቂቶቹን ያነሣሣን እንደሆነ ፡—

፩/ ኖኅ የተባለው አባት ፣ ይኸ አባት ቤተሰቡን ሠርቶ ቀጥቶ ከመ ኖሩ የተነሣ በመላ የሰው ልጅ ሁሉ በጥፋት ውሃ ሲቀጣ ራሱን ቢተሰቡ ንም ለማዳን ችሏል ። ልጆቹ ስሕተት ሠርተው በደልም ፈጽመው እን ዳይፈርድባቸው በማለት እንደ ካህን ሲጸልይላቸው ፣ መሥዋዕትም ሲሠ ዋላቸው እናገኛለን (ዘፍ ፡ ፰ ፡ ፳) ።

፪/ አበ ብዙኃን አብርሃም ፣ እርሱም እንዲሁ የቤተሰብ አባትና አስተዳዳሪ እንደመሆኑ እንደ ካህን ቤተሰቡን ሲመክር ሲያስተምር በመ ልካም ሥነ ሥርዓት ሲመራ ፣ መሥዋዕትም ሲሠዋ ይገኛል (ዘፍ ፳፪፡ ፲፫) ።

፫/ የዘለዓለም ካህን የተባለው መልከ ጼዴቅ ፣ ይኸ ሰው ትውልዱ ነገዱ አይታወቅም እንጂ ካህን በሌለበት ዘመን ካህን ሆኖ ኅብስተ አኮ ቴት ጽዋዓ በረከት አቅርቧል (ዘፍ ፡ ፲፬ ፡ ፲፰) ።

፬/ የሙሴ አማት ዮቶር ፣ ይኸ ሰው የምድያም ካህን እየተባለ ይጠራ ነበር ፤ ቤተሰቡንም ያስተምር ይመክር ነበር ፤ ጸሎት ይጸልይ መሥ ዋትም ይሠዋ ነበር (ዘጸአ ፡ ፳፰ ፡ ፪) ።

፭/ መስፍኑ ሙሴ ፣ የእስራኤል መሪ አስተማሪ የሆነው ሙሴ እስ ራኤልን በመንፈሳዊም በሥጋዊም አመራር እየመራ ሕዝቡን ሕዝበ



እግዚአብሔር አሰኝቷል ፤ እርሱም የአምላክ ባለሟል ተብሏል ፤ እንደ ፓትርያርክ (ሊቀ ካህናት) ሆኖ አሮንንና ልጆቹን ካህናት ይሆኑ ካህናትም ይባሉ ዘንድ ቀብቷል ፣ ሹሟል ።

ከዚህ በኋላ ግን የብሉይ ኪዳን ክህነት ተጀመረና የክህነት ወገን የክህነትም ቤት የአሮን ቤት ሆነ፤ የእርሱ ልጆች የልጅ ልጆቹም ሁሉ ካህ ናት እየሆኑ ካህናትም እየተባሉ የብሉይ ኪዳን የክህነትን ተግባር ሲፈ ጽሙ ኖረዋል ።

የአሮንና የልጆቹ የክህነት አገልግሎት ሁሉ ለሐዲስ ኪዳን ክህነ ታዊ አገልግሎት ምሳሌ ሆኗል ።

## ፫/ የብሉይ ኪዳን ካህን ፤

እግዚአብሔር አምላክ የሁሉ ፈጣሪ የሁሉም አስገኝ እንደመሆኑ ነገሩም ሁሉ ገንዘቡ ነው ፤ ስለዚህ ሕዝቡን እርሱ የሚጠብቅ የሚመለ ከት ሲሆን እንደ እርሱ ሆኖ ከእርሱ በታች የሚጠብቅለት ከሰው ወገን ካህን አድርጎ አስነሣ ። ነቢዩ ሙሴ በእስራኤል ላይ መስፍን ሆኖ ሲነሣ በቤቱ የታመነ መሪ ፣ የታመነም አስተዳዳሪ በመሆን ነው ። ይኸንንም ቅዱስ ጳውሎስ ሲመሰክርለት «ሙሴም በቤቱ ሁሉ የታመነ ሆኗልና እንደሎሌ ለምስክር ኋላ ይነግር ዘንድ ባለው ነገር (ዕብራ ፡ ፫ ፡ ፬) ።

ሙሴ የእስራኤል መሪ ይሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር ሲጠራ የፈር ዖን ልጅ ሆኖ በሰው ዘንድ ከብሮ ከመኖር ይልቅ ከሕዝቡ ጋር መከራን ይቀበል ዘንድ ስለወደደ የፈርዖን ልጅ ነህ ቢሉት አይደለሁም ሲል ካደ። ይኸንንም ሐዋርያው ጳውሎስ «ሙሴ ከአደገ በኋላ የፈርኦን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እንቢ አለ ፤ ከግብጽ ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስ ቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ እንደሆነ አስቧልና ፤ ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራን መቀበልን መረጠ ፤ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቷልና» ሲል በሰፊው ገልጦ ጽፎለት እናገኛለን (ዕብራ ፡ ፲፩ ፡ ፳፬—፳፮) ።

ሙሴ በእግዚአብሔር የታመነ መስፍን በመሆኑ ሕዝበ እግዚአብ ሔር የተባለውን እስራኤልን እየመራ ከባርነት ወደ ነፃነት ፣ ከባዕድ አገር ወደ ምድረ ርስት ይዞ ገብቷል ።

ሙሴ እንደ መስፍንም እንደ ካህንም እየሆነ ሕዝቡን ሲመራ ፣ ሕዝቡ ባጠፋም ጊዜ ሲገሥጽ ፣ ሲመክር ቆይቷል ። የሕዝቡን ጩኸት ወደ እግ



www.ethiopianorthodox.org

ዚአብሔር ያሰማ የእግዚአብሔርንም ምሕረት ደግሞ ወደ ሕዝቡ ያስተላ ልፍ ነበር ።

እስራኤል ተሳስተው ጣዖት ቢያመልኩ ለራሱ ነፍስ ሳይሳሳ ሙሴ እሥራኤልን ቀጥቷል፥ አምልኮተ ጣዖትን አጥፍቷል (ዘጸአ ፡ ፴፪፥ ፳፯—፳፰) ።

ሙሴ እንዲህ እያደረገ ክህነትን ከምስፍና ጋር ይዞ ሲቆይ እግዚአ ብሔር አምላክ ክህነትን ለአሮንና ለቤተሰቡ ስለ ሰጠው አሮንን ካህን አድርጎ ሹሞታል ። ከዚያ በኋላ ክህነት ከአሮን ዘር እንዳይወጣ፥ የአሮን ነገድ ወንድ የሆነው ሁሉ ካህን እንዲሆን ካህንም እንዲባል ተደነገገ ።

ስለዚህም እግዚአብሔር አምላክ ሙሴን እንዲህ ሲል አዘዘው «አን ተም አሮንን ወንድምህን ልጆቹንም ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይ ተህ ወደ አንተ አቅርብ ፤ ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ ፥ አሮንን ፥ ናዳብን ፥ አቢሁንም ፡ አልዓዛርንም ፡ ኢታምርንም፥ የአሮንን ልጆች» (ዘጸ፥ ፳፰፥፩)።

አሮንም የሙሴ ታላቅ ወንድም የሆነው የመጀመሪያው የብሉይ ኪዳን ካህን ሆነ ፥ ከእርሱም ባለሟልነት የተነሣ ልጆቹ የልጅ ልጆቹ ሁሉ በእርሱ እግር እየገቡ ካህናት እንዲሆኑ ካህናትም እንዲባሉ ሆነ ። ሥራቸውም መሥዋዕት መሠዋት እግዚአብሔርን ማምለክ ፤ የሕዝቡን ኃጢአት ማስተስረይ ፤ የኪዳኑን ጽላት መሸከም ሌላም ይኸን የመስለ ነበር ። እነዚህ የብሉይ ኪዳን ካህናት የእግዚአብሔር ኃይል መገለጫ የሥልጣኑ መታወቂያ በመሆን ለምጽ የሚያነጹ ፥ ደዌ የሚፈውሱ ፥ ርኩ ሱን ሁሉ የሚቀድሱ ነበሩ ። ካህናት በጦር ሜዳም የኪዳኑን ታቦት በመ ሸከም ሳይፈሩ ከሠልፉ የሚውሉ ነበሩ ፤ እነርሱም ታቦተ ኪዳኑን ተሸ ክመው በጦር ሜዳ በዋሉ ጊዜ እስራኤል በአቸናፊነት ከብረው ይመለሱ ጠላት ግን አፍሮና ድል ሆኖ ይገባ ነበር ። እንዲሁም የዮርዳኖስን ወንዝ እስራኤል በተሻገሩ ጊዜ ካህናት ጽላተ ኪዳንን ተሸክመው ከወንዙ መካ ከል ገብተው በመቆማቸው ወራጁ ውሀ ቆመላቸው ፤ ስለዚህ ሕዝቡ በደ ረቁ ተሻገረ ። የኢያሪኮንም ከተማ ለመያዝ ሙከራ በአደረጉ ጊዜ ጽላተ ኪዳንን የተሸከሙ ካህናት የኢያሪኮን ቅጽር ፯ ጊዜ በመዞራቸው ቅጽሩ ፈረሰ ፤ እስራኤልም ገብተው ወጓቸው ድልም አደረጓቸው (ኢያሱ ፥ ፮ ፡ ፩—፳፮) ።

ካህናት ከዘመን ወደ ዘመን የተሸጋገሩትን ያህል በቍጥር እየበዙ በማዕርግም እያደጉ በመሄዳቸው ሊቀ ካህናት ወይም ሊቃነ ካህናት እስ መባል ደርሰው ነበር ።

በነዚህ ካህናት አንጻር ደግሞ ሊዋውያን የሚባሉ ነበሩ ፤ እነርሱም የሌዊ ልጆች ናቸው፤ ስለዚህ በሌዊ ሊዋውያን ተብለዋል።እነዚህም ነገዶች እስራኤል ጣዖት በአመለኩ ጊዜ አሮን ሕዝቡን በመፍራት ሳይከላከል በመቅረቱ እግዚአብሔር አምላክ ተቆጥቶ ለእርሱና ለልጆቹ ተቃ ራኒዎች የሆኑ ነገዶች እነዚህን ሊዋውያንን አስነሣበት። ጣዖት ያመለከውን ሕዝብ ሙሴ በቀጣበት ጊዜ ሌዊና ልጆቹ ተባብረውት ነበር ፤ ስለዚህ ይህ ክብ ርና ስም ተሰጣቸው (ዘጸ ፥ ፴፪ ፡ ፳፯—፳፰) ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሌዊ ልጆች እንደ አሮን ልጆች ካህናት ሆነው ካህናትም መስለው መታየት ጀመሩ ፤ ዋና ሥራቸው ግን ደብተራ አሪ ቱን ማገልገል ፥ ንዋየ ደብተራውን መሸከም ነው ። ይኸንም የሚያመለ ክት እግዚአብሔር አምላክ ያሰማውን ድምፅ እንዲህ ሲል እናገኛ ለን «እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው እንዲህ ሲል የሌዊን ነገድ አት ቍጠረው ቍጥራቸውንም ከእስራኤል ልጆች ጋር አታድርግ ። ነገር ግን በምስክሩ ድንኳን ላይ ሌዋውያንን አቁማቸው ፤ በዕቃውም ላይ ሁሉ በእርስዋም በሚሆነው ነገር ሁሉ ላይ እርሳቸው ድንኳኒቱን ይሸከሙ ፤ ዕቃውንም ሁሉ፤እርሳቸውም ያገልግሏት ፤ በድንኳኒቱም ዙሪያ ይሥፈሩ» (ዘኍል ፥ ፩ ፡ ፵፯—፶ ) ።

ይኸ የብሉይ ኪዳን ሥርዓት እስከ ክርስቶስ ዘመን ሠራ ፤ ለሐዲስ ኪዳንም አምሳል መርገፍ ሆነ ፤ ምንም መጀመሪያውን የፈቀደው የደነገ ገው እግዚአብሔር አምላክ ቢሆንም ሕጉን በሕግ በአደሰው ጊዜ ለሐዲስ ኪዳን ካህን ጀማሪ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ ።

እውነተኛው ሊቀ ካህናት እርሱ ሆነ ፤እርሱም መሥዋዕት የሚሠዋ፥ መሥዋዕትም ሆኖ የሚቀርብ በትክክልም የሕዝቡን ኃጢአት የሚያስተ ሰርይ ሆኖ ቀረበ ።

## ፪/ የሐዲስ ኪዳን ካህን ፥

እግዚአብሔር አምላክ ለሕዝቡ መሪዎች አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ ካህናት እንዲሾሙ ቢያደርግም ካህናቱ ተግባራቸውን ከመርሳታ ቸው የተነሣ ሕዝቡ ጠባቂ እንደሌለው መንጋ ባዘነ ፥ ቃባ እንደያዘውም በግ ተቅበዘበዘ ። ሕዝቡን ራሱ በፈቀደ ጊዜ እግዚአብሔር ወልድ ልዑል ባሕርዩን ዝቅ አደረገ፤ማለት ከሰማየ ሰማያት ወረደ ከድንግል ማር ያም ተወለደ ።



www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን ኢየሱስ የ፴ ዓመት ዕድሜ ሲሆነው ሰው የሆነበትን ዓላማ
ለመፈጸም ማስተማር ጀመረ ፤ በዚህም ጊዜ ደከመኝ ልረፍ ፣ በዛብኝና
ሰለቸኝ ስለዚህ ልተወው ሳይል ማስተማሩን ፣ ሕዝብንም ማገልገሉን
ሳያቋርጥ የካህንነቱን የሊቀ ካህንነቱን ተልእኮ ፈጸመ ።

የሰው ልጅ በሠራው ኃጢአት ተፈርዶበት ከተሰጠው ቅጣት
ለማዳን እግዚአብሔር ወልድ በሰው እግር ገብቶ ለመሞት ፈቀደ፤ ሰው
ራሱን ለማዳን ከማይችልበት ደረጃ ደርሶ ነበርና ። ሰው የፈለገውን ያህል
ደም ቢያፈስ ፤ ስብ ቢያጤስ ፤ መሥዋዕትም ቢሠዋ ከቶ ሊድንአልቻለም
ነበርና ፤ ስለዚህም ሕዝቡን ለማዳን በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት አንጻር
እርሱ እውነተኛው ሊቀ ካህናት ሆኖ ቀረበ ። ሊቀ ካህናት የሚባለውንም
ስም ገንዘብ አድርጎ ራሱን ሠዋ ።

ሊቀ ካህንነቱም እንደ አሮን ልጆች እንዲሁም እንደሌዊ ልጆች
ከዘር ሲወርድ ሲወራረድም የመጣለት አይደለም ፤ እርሱም እንደ ብሉይ
ሊቀ ካህናት መሥዋዕት ያቀረበ አይደለም ፤ ለማዳን ችሎታ ያለው ሊቀ
ካህናት እንደመሆኑ ለማዳን የሚችለውን ራሱን መሥዋዕት አድርጎ አቀ
ረበ እንጂ (ዕብራ ፥ ፱ ፥ ፲፬—፲፰) ።

ክርስቶስ ዘለዓለማዊ ሊቀ ካህናት ሆነ ፤ ስለዚህም ነቢዩ ዳዊት አስ
ቀድሞ «አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ» ሲል ተናግ
ሮለታል (መዝ. ፻፱ ፥ ፬ ፥ ዕብራ ፥ ፯ ፥ ፳) ። ሊቀ ካህናችን ኢየሱስ የመ
ጣበት የካህንነቱን ተልእኮ በዚህ መልክ ፈጸመ ፤ የሐዲስ ኪዳንም የመ
ጀመሪያው ሊቀ ካህናት ሆነ ፤ የእውነተኛው ካህን ምሳሌ በመሆን አስ
ተማረ ፤ በቃል ያልተማረውንም በሥራ ተርጉሞ አሳየ ። ክርስቶስ እው
ነተኛና ዘለዓለማዊ ሊቀ ካህናት እንደመሆኑ የእርሱ ተከታዮች የሚሆ
ኑትን እርሱን መስለው የሚሠሩትን ሐዋርያትን መረጠና በእግሩ ተካ
ቸው ፤ ለመረጣቸው ሐዋርያትም ፍጹም ክህነታዊ ሥልጣንን ሰጣቸው ፤
በሁሉም ላይ አሠለጠናቸው (ማቴ ፥ ፲ ፥ ፩) ።

ቅዱሳን ሐዋርያትም መምህራቸው ክርስቶስ «ሑሩና አሕዛብን
ሁሉ አስተምሩ፤ ስታጠምቋቸውም በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም»
ሲል ያዘዛቸውን በመከተል በዓለም ተበትነው የዛሬው ካህን የእነሱ
ተተኪ ሁኖ ሊሠራውና ሊፈጽመው የሚገባውን ተልእኮ በትክክል
ፈጸመ ። (ማቴ ፥ ፳፰ ፥ ፲፱) ።



እነዚህ ሐዋርያት የተሰቀለውን ክርስቶስን ማዕከል በማድረግ በማ ፤
ስተማር ፤ ጸሎት በመጸለይ ፤ መሥዋዕት በማቅረብ ፤ በሽተኞችን በመፈወስ
በጠቅላላም ክህነታዊ አገልግሎትን በመፈጸም ሠሩ ።

ሕይወቱ ተበላሽቶ የነበረውን ሕዝብ ከብሉት ወደ ተሐድሶ ለወ
ጡት ፤ ማኅበራዊ ኑሮው መራራ የነበረውን አጣፈጡት፤በጠቅላላም ሁሉን
ከሞት ወደ ሕይወት መለሱት ።

ለሐዲስ ኪዳን ካህን ሁሉ መሥራች ኢየሱስ ክርስቶስ እንደመሆኑ
የእርሱን ፈለግ ተከትለው ተልእኳቸውን በመፈጸም ለክህነታዊ አገል
ግሎት ፍጹም ሠራተኞችና ምሳሌ ሆነው ቅዱሳን ሐዋርያት ሠሩ ።

ከሐዋርያት ጀምሮ ለክህነት ማዕርግ ብቁ የሆኑት እየተመረጡ
ተሹመው አገልግሎታቸውን የፈጸሙ ብዙዎች ናቸው ። ከዚያን ጊዜ
ጀምሮ ክህነት ቅዱስ አገልግሎት በመሆኑ ከእግዚአብሔር ጥሪ የደረሰው፤
ቤተ ክርስቲያንም የመረጠችው፤ ለዓላማውም ብቁ ሆኖ የተገኘው ሰው
ካህን እየሆነ ፣ በአንብሮተ እድም እየተሾመ ፤ ተልእኮውን እየፈጸመ ሳያ
ቋርጥ እስከ ጊዜያችን ደርሷል ።

---

## ፩/ ለክህነት አገልግሎት መጠራት ፤

ማንኛውም ሰው ለአንድ ሥራ ጥሪ ወይም ስጦታ አለው ፣ ይህም
ስጦታ የተፈጥሮ (የባሕርይ) ሊሆን ይችላል ፤ ወይም በትምህርትና በል
ማድም ይገኛል ፤ ይህም ነገር እርግጠኛ መሆኑን የሚያስረዳ አንድ ሰው
አንድ ነገርን ይወዳል ሌላውን ግን ይጠላል ፤ አንደኛውን አዘውትሮ
ይሠራል፤ ስለርሱም ይናገራል ፤ ሌላውን ግን ሊያየው ቀርቶ ሊሰማው
አይወድም ። ይህ የመውደድና የመጥላት ስሜት ኃይል «ጥሪ ወይም
ስጦታ» ይባላል ። የተፈጥሮ ስጦታ ወይም ጥሪ የተባለው የማይናወጥ
ልባዊ ስሜት ሆኖ እናገኘዋለን ። የተፈጥሮ ስጦታ ወይም ጥሪ በትምህ
ርት ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለና እያደገ እየተስፋፋም የሚ
ሄድ ነው ፤ ስለዚህ አንድን ሕፃን ከልጅነቱ ጀምሮ በዚህ ስጦታ ሊመሩ
ትና ሊያሳድጉት ይገባል ፤ በዚህ ዓለም ልዩ ልዩ አይነት የሆኑ ዕውቀቶ
ችና ጥበባት ይገኛሉ ፤ የሰውም ስጦታው እንዲሁ የተለያየ በመሆኑ አንዱ
የሚወደውንና የሚያዘወትረውን ሌላው አይወደውም ፤ ስለ ርሱም ፍላ
ጎት ከቶ የለውም። ይህንም ይዘው የቀደሙ አቴናውያን ሕፃናት በመረጡት
እንዲያድጉ በማለት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ የሚሠሩትንና የሚናገሩትን
ጠንቅቀው ይከታተሏቸው በዚያውም ያሳድጓቸው ነበር ይባላል ። ካህ

ንም የሚሆን ሰው እንዲሁ የተፈጥሮ ስጦታና ጥሪ ሊኖረው ይገባል ፤ ምክንያቱም የሕዝቡ መሪ ፤ የትሩፋት አበጋዝ ፤ የነፍሳቸውም ጠባቂ ፤ የመልካምም ሥራ ሁሉ አብነት ስለ ሆነ አንድ ጊዜ ከጀመረ ወደ ኋላ ሊመለስ ከቶ የማይችል ነውና ስለዚህ «ኢየሱስም አለ ማንም የለም ማረሻ በእጅ ይዞ ወደ ኋላው የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት ይሆን ዘንድ» ሲል ይነግረናል (ሉቃ ፡ ፱ ፡ ፷፪) ።

ካህኑ ይህን ለማለፍ ለሥራውም መልካም ውጤትን ለማግኘት የሚችለው ቀድሞውን ጥሪ ሲኖረው ከእግዚአብሔርም ሲታዘዝ ነውና ።

ይህ ጥሪ ሰማያዊ የሆነ ሰማያዊም አገልግሎት ያለው ፤ በሚገባም ቢፈጽሙት ሰማያዊ ዋጋን የሚሰጥ ስለ ሆነ ብዙዎች አክብረው ይቀበሉታል፤ እንደ ጥሪያቸውም ለመፈጸም ተጋድሎን ያደርጋሉ ። ይኸ ጥሪ ወይም ስጦታ የተባለው ሀብት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ወይም የሚጠራ ማለት ነው ። በብሉይ ኪዳን አርእስተ አበው የተባሉት እነ ሙሴ በመላም ነቢያት ከእግዚአብሔር ዘንድ እየተጠሩ ሀብተ ትንቢት እየተሰጣቸው ተልእኳቸውን ፈጽመዋል ። በሐዲስ ኪዳንም በክርስቶስ የተጠሩ በመላ ሐዋርያት እንደ ጳውሎስ ፤ ሰብዓ አርድእት ይህንም የመሰሉ ብዙዎች ናቸው ። ይህ ዐይነት ጥሪ ግን በሁለት ይከፈላል ይኸውም አንደኛው ውስጣዊ፤ሁለተኛው አፍአዊ ጥሪ ይባላል ።

<u>ሀ/ ውስጣዊ ጥሪ</u> የተባለው በተፈጥሮ የሚሰጥና የሚጠራ የሰው አሳቡ የሚያዘነብልበት በዚያውም ጸንቶ የሚኖርበት ከትምህርትም ጋራ የተከታተለው እንደሆነ መልካም ውጤትን የሚሰጥ ጥሪ ወይም ስጦታ ነው ።

ይህ ጥሪ ወይም ስጦታ ለማንኛውም ሥራ ለማንኛውም ጥበብ የሚሰጥ ነው፤ በተለይ ግን ሊጠንቀቁለት የሚገባ ለክህነት ማዕርግ ነው ፤ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ስጦታ ወይም ጥሪ ያለው ራሱም ወዶና ለምዶ የገባው ካህን ምንም ጊዜ ልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራ ቢደርስበት አይሰቀቅም አይመረርም ፤ እንዲያውም ደስ እያለው በመከራ ላይ መከራ ቢጨመርበት ጸጋ እንዲበዛለት አምኖ ይቀበለዋል ፤ (፪፡ ቆሮ፡ ፲፪ ፡ ፱—፲ ፡ የሐ ሥራ ፳ ፡ ፳፯—፴፪) ።

ጥሪ ሳይኖረው ራሱም ሳይወደው የገባ እንደ ሆነ ግን በየጊዜው ሲመረር ፤ ሲበሳጭ ፤ ለራሱ ቀርቶ ለሌሎችም የመሰናክል ድንጋይ ይሆናል ፤ ስለዚህ ካህን የሚሆን ሰው ሰውነቱን ይመርምር ፤ ጥሪውን ያክብር ፤



የኃላፊነቱን ከባድነት የሥራውን ብዛት አጥንቶ ይግባ። ጥሪ ወይም ስጦታ እንዲኖረው የፈለገ እንደሆነ ደግሞ አስቀድሞ ልባዊ ጸሎት ያድርግ፤ለማንኛውም ሥራ ተስማሚ እንዲሆን እግዚብሔርም እንዲፈቅድለት «ወይኩን ፈቃድከ» እያለ ይጸልይ፤ጸሎት የበር ሁሉ መክፈቻ የማትሰበር ቁልፍ ናትና ፤ ስለዚህ ያለማቋረጥ ይጸልይ ፤

ክርስቶስ እንኳን ሐዋርያትን ለዚህ ሥራ ሲመርጥ አስቀድሞ ወደ ተራራ ወጥቶ ጸሎት ጸልዮ ነው « ሆነም በዚያች ወራት ወደ ተራራ ወጣ ጸሎት ይጸልይ ዘንድ በእግዚአብሔር ጸሎትም ተግቶ ነበር ሌሊቱን ሁሉ ቀንም በሆነ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን ጠራ ከእርሳቸውም ዐሥራ ሁለት መረጠ ሐዋርያት ያላቸውን» (ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፲፪—፲፫)

ይህም የሚያስረዳን ለሿሚም ለተሿሚም አስቀድሞ ጸሎት ማድረግና ጥሪውን ወይም ስጦታውን ማግኘት እንዳለበት ነው ፤ ከዚህም በቀር ካህኑ ከዚያን ቀን ጀምሮ ሥራው ጸሎት እንደሆነ እንዲረዳው ነው (፩፡ ጢሞ፡ ፪ ፡ ፩—፫) ።

<u>ለ/ አፍአዊ ጥሪ</u> ፡— አፍአዊ ጥሪ ማለት እንዲሁ ከውጭ የሚሰማ ድምፅ ነው ፤ ይህ እንደ ገና በሁለት ክፍል ይከፈላል ፤ ቀጥተኛ አፍአዊ ጥሪና በጐን የሚሆን አፍአዊ ጥሪ ናቸው ።

ቀጥተኛ ጥሪ ማለት በቀጥታ ከእግዚአብሔር የሚጠሩት ጥሪ የሚሰሙትም ድምፅ ማለት ነው ። እግዚአብሔር ሕዝቡን ያለ ጠባቂ ከቶ ትቶት አያውቅም ስለዚህም የርሱ እንደራሴዎች ሆነው በታማኝነት የሚጠብቁለትን ሲጠራና ሲመርጥ ድምፅም ሲያሰማ ይኖራል ።

ለምሳሌ ፡— በብሉይ ኪዳን ፣ ሙሴን ፣ ኤልያስን ፣ እንዲሁም በመላ ነቢያትን ሕጉን የሚያስተምሩለትን ትንቢት የሚናገሩለትን ሕዝቡን የሚያስተዳድሩለትን ጠርቷል (ኦሪት ዘፀአ ፡ ፫ ፡ ፬—፳፪) ።

በሐዲስ ኪዳንም በመላ ሐዋርያትን ጠርቷል (ማቴ ፡ ፲ ፡ ፩—፭) ። ሰብዓ አርድዕትንም ሌሎችንም አገልጋዮች ራሱ ጠራቸው (የሐ ፡ ሥራ ፬ ፡ ፬—፳፮)።«እርሳቸው ም በእግዚአብሔር ሲያገለግሉ ሲጾሙም ፡ መንፈስ ቅዱስ አለ በርናባስንና ሳውልን ለዩልኝ ለጸራኋቸው ሥራ በዚያን ጊዜም ጾሙ ፤ ጸልዩም ፤ እጃቸውንም በጫኑባቸው ጊዜ ሰደድዋቸው»

(የሐ ፡ ሥራ ፡ ፲፫ ፡ ፪—፫) ። የሐዋርያትን ጥሪ ራሱ ሲያጸድቀው «እናንተ አልመረጣችሁኝም እኔ እላንተን መረጥኋችሁ እንጂ አስነሣ



www.ethiopianorthodox.org

ኋችሁም ትሄዱ ዘንድ ፍሬም ታፈሩ ዘንድ ፍሬያችሁም ይኖር ዘንድ» ሲል ጌታ አስረድቷል ፤ (ዮሐ ፡ ፲፮ ፡ የሐ ፡ ሥራ ፡ ፩ ፡ ፳፱—፳፬) ።

እንደዚህ እያደረገ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊ፤ ጠባቂ፤ አበንፍስ የሚሆኑትን ሁሉ እግዚአብሔር ሲጠራቸው እናገኛለን ፡ ይህም ቀጥተኛ ጥሪ ይባላል ። ቀጥተኛ ያልሆነ አፍአዊ ጥሪ ማለት ደግሞ ከራሱ ከእግዚአብሔር በቀጥታ ከላይ እንደዘረዘርነው ሳይሆን በጐን በሕልም በሰው ወይም በቤተ ክርስቲያን አማካይነት የሚጠሩት ጥሪ ነው ። በቤተ ክርስቲያን አማካይነት የሚጠሩት ጥሪ ለምሳሌ ፡ በርናባስንና ማትያስን በምግባር በሃይማኖት ፍጹም ሆነው ቢያገኗቸው ሐዋርያት መረጥዋቸው «ሁለትም አቆሙ፤በፊታቸው ዮሲፍን በርናባስ ተብሎ የሚጠራውን ዮስጦስ ተብሎ የሚጠራውንም ማትያስን በጸለዩም ጊዜ አሉ ፤ አንተ ጌታ ሆይ የሁሉን ልብ የምታውቅ ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ግለጥ የመረጥከውን የዚህችን ማገልገል የመልእክቲቱን ሥፍራ ይወስድ ዘንድ ይሁዳ የተዋትን ወደ ሥፍራው ይሄድ ዘንድ ዕጣውም በማትያስ ላይ ወደቀ ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋራም ተቈጠረ (የሐ ፡ ሥራ ፡ ፩ ፡ ፳፫—፳፮) ፤

ይህንም የመሰለ በቤተ ክርስቲያን የሚደረግ ጥሪ እስጢፋኖስንና ሌሎችን ስድስቱን ዲያቆናት እናገኛለን (የሐ ፡ ሥራ ፡ ፫ ፡ ፳) ።

ቀጥተኛ ከእግዚአብሔር ያልሆነ አፍኣዊ ጥሪ ይህ ነው፤ እንደዚህ ያለ ጥሪ ወይም ምርጫ ለካህናት የኖራቸው እንደሆነ የሥራቸው እርምጃ ከዕለት ወደ ዕለት እየጎላ ይሄዳል ፤ ተልእኳቸውንም በሚገባ ይፈጽማሉ ።

## ፯/ ክህነት ቅዱስ ማዕርግ እንደሆነ ፤

ከቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ፩ኛው ከፍተኛውም ፡ ማለት ሌላውን ምሥጢር ሁሉ የሚቀድስና የሚያነጻ ምሥጢረ ክህነት ነው ። ምሥጢረ ክህነትን ተቀብለው በሚገባ ተልእኳቸውን የሚፈጽሙ ካህናት ሁሉ የቅዱሱ የእግዚአብሔር እንደራሴዎች ስለሆኑ ቅዱሳን ይባላሉ ።

የሐዲስ ኪዳን ክህነት መሥራች ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ እርሱ ቅዱስ እንደመሆኑ መዓርጉም ቅዱስ ነው ።

ካህናት የተመረጡ ወገኖች ፡ የተቀደሱ ዘሮች እንደሆኑ ቅዱስ ጴጥሮስ «እናንተ ግን የመንግሥትና የክህነት ወገን ናችሁ ፤ የተቀደሳችሁም ዘር ለርስት የተለየ ሕዝብ - - - » ሲል አስረድቷል (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲) ።



ካህናት ከፍተኛ ማዕርግ ቅዱስ ሥልጣን ስላላቸው የማሠርና የመፍታት ሥልጣን አላቸው ፤ ይኸንኑም ክርስቶስ ሲመሰክርላቸው« ይኸንንም ብሎ እፍ አለባቸው ፤ አላቸውም መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ ኃጢአቱን የተዋችሁለት ቀረችለት ፤ የያዛችሁበትም ተያዘችበት » ሲል በሰፊው አስረድቷል (ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፳፪—፳፫) ።

ለቅዱሳን ሐዋርያት ቅድስናቸውን አረጋግጦ እርሱም ቀድሶ አባቱም እንዲቀድሳቸው «ቀድሶሙ በጽድቅከ» ሲል ጸልዮላቸዋል ፤ ስለዚህ ካህን በምድር ያለ መልአክ ነው ፤ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ምስጋና የሰጠ ሁል ጊዜ እንደ መላእክት ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ እያለ የእግዚአብሔርን ስም እየቀደሰ ይኖራልና ።

ቅዱስ ጳውሎስ በየጊዜው የሚነሡትን ካህናት ቅዱሳን ሲላቸውና ቅዱሳንም መሆን እንዲገባቸው ሲናገር «ስለዚህም ቅዱሳን ወንድሞቼ ሆይ ከሰማይ በመጣችው መጠራት ባልንጀሮቼ ይኸን የሃይማኖታችንን ሐዋርያ የካህናትንም አለቃ ተመልከቱ ኢየሱስ ክርስቶስን » ሲል ገልጦ ጽፎ እናገኘዋለን (ዕብራ ፡ ፫ ፡ ፩) ።

ክህነት ቅዱስ ማዕርግ ከፍተኛም ሥልጣን ሲሆን ማንም በዘር ሊወርሰው በገንዘብ ሊገዛው አይችልም ፤ እግዚአብሔር አምላክ ለጠራውና ለዚህ ትበቃለህ ላለው ብቻ ነው እንጂ (የሐ ፡ ሥራ ፡ ፰ ፡ ፲፱—፳፬) ። ማዕርገ ክህነት ለመላእክት እንኳን ያልተሰጠ ለሰው ልጅ የተሰጠ ማዕርግ ነው ፤ ዘኢተገብረ ለመላእክት ተገብረ ለካህናት ሲል ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተናግሯልና ።

ቅዱስ ጳውሎስ በቅዱሳን መላእክት ላይ እንኳን ካህኑ ሥልጣን እንዳለው ሊፈርድም እንደሚችል ሲናገር «ወይስ አታውቁምን እኛ በመላእክት እንድንፈርድ ፡ እንዴት ይገባን ፡ በዚህ ዓለም ነገር መፍረድ» ሲል አስረድቷል (፩ ፡ ቆሮ፡ ፮ ፡ ፫) ።

ክህነት ቅዱስ ማዕርግ በመሆኑ ካህኑ በምድር የወሰነውን እግዚአብሔር በሰማይ ያጸድቀዋል ፤ ካህኑ ከእግዚአብሔር የተጣላውን ሰው ጸልዮ መሥዋዕትም ሠውቶ ሰውየውን ወደ ንስሓ አስገብቶ ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቀዋል ።

የክህነት ማዕርግ እንዲህ ያለ ቅዱስና ክቡር ሲሆን ለዚህ ማዕርግ ተቀባይ የሚሆነው ሰውም በጣም የበቃ ለማዕርጉ የተስማማ መሆን አለበት ።



www.ethiopianorthodox.org

## ፯/ የካህኑ መለያ ምልክት ፤

ምንም ለሐዲስ ኪዳን ካህን ጀማሪው ኢየሱስ ክርስቶስ ቢሆን እርሱም እውነተኛውን ክርስቲያናዊ ሕይወት የኖረና ምሳሌነቱን የሰጠ ቢሆን ፡ ተከታዮቹ ሐዋርያትም በዚያው መንፈስ ቢመሩም የኋላ አባቶች ነገሩን በማጠንከር በምርጫው ጊዜም የበለጠ ጥንቃቄ እንዲደረግበት በኋላም በልብሱ ፡ በቆቡ ፡ በመስቀሉ ፣ በሌላም ይኸን በመሳሰሉ መለያ ዎች ካህኑ እንዲታወቅ፤ከሌላውም ሰው እንዲለይ ወስነዋል ። ይሁን እንጂ ልብስ ሰውየውን ካህን ስለማያደርገው ውስጣውያን መለዮች እንዲኖሩትና በነዚያ መጠበቅ እውነተኛው ካህን ተለይቶ እንዲታወቅ ተደርጓል ። ለእውነተኛው ካህን መለያ መታወቂያም ከሚሆኑት ብዙዎች ውስጥ የሚከተሉትን ፯ቱን እንደ ዋና አድርገን እናቀርባለን ።

፩ኛ/ ፍጹም ሃይማኖት ፡— ካህኑ የሥራው ሁሉ መጀመሪያ መፈጸሚያም ሃይማኖት ነው ፤ ማለት በእግዚአብሔር ፈጣሪነት ሁሉ እንደተፈጠረ፣ ሁሉንም እግዚአብሔር እንደሚቆጣጠረው ፣ ሁሉንም እግዚአብሔር እንደሚያውቀው ማመን ለካህኑ ጌጌታው ነው። የሁሉም ፈጣሪ የሁሉም አስገኚ እግዚአብሔር ነው ፤ የሆነውና የሚሆነው ሁሉ እርሱ ሳያውቀው እርሱም ሳይፈቅደው ከቶ አይደረግምና ። ይኸም ዓይነት እምነት የካህኑ ብቻ ሳይሆን የሰው ሁሉ ዋናውና ዘላቂው እምነት ነው ፤ የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር እንደሆነ ካህኑ በፍጹም ልቡናው ከአመነ፤ ሁሉንም የሚቆጣጠር እርሱ ብቻ መሆኑን ከዐወቀ፤ በተግባሩ የበረታ ፣ የማይፈራ ፣ የማያፍር ፣ ከእውነትም ፈቀቅ የማይል ይሆናል ፤ ምክንያቱም ክፉ ቢሠሩ ፍዳ ፣ በጎ ቢሠሩ ዋጋ የሚከፍል እርሱ ብቻ መሆኑን አምኖ ይሠራልና ። ካህኑ የእርሱ ብቻ አገልጋይ ይሆናል ፤ ከእርሱም ብቻ ዋጋ ለማግኘት ይጠብቃል ፤ ያለዚያ ጊዜያዊውን ክብር ከጊዜያዊ ሰው ይጠብቃል ፤ ሰውን የሚያመልከው ፤ ሰውን የሚፈራው ሁሉ ኃላፊውን ክብር ለጊዜው ያገኝ ይሆናል ፤ ያውም ሁል ጊዜ አይሆንም ፤ ቀጥሎም ሿሚውም ተሿሚውም ሰዎች እንደመሆናቸው አብረው ያልፋሉ ።

ክብሩም ሹመቱም አብሮ ያልፋል ፤ ስለዚህ ነዋሪው ቀዋሚው ካህኑ ኃላፊ ሆኖ ይቀራል ማለት ነው ። ነገር ግን በእግዚአብሔር አምኖ እርሱን ምስክር አድርጎ የሚሠራ እንኳን ካህኑ ማንም አማኒ ቢሆን ክብር አለው ፤ ለሥራውም መልካም ውጤት አለው ።

በእግዚአብሔር አምኖ የሚጀመር ሁሉ መልካም ፍጻሜ አለው ፤ ሁሉን ለማድረግ ችሎታ ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነውና ፤ ገበሬው



በእግዚአብሔር አምኖ ዘሩን ከጎተራ አውጥቶ ይዘራል ፣ ነጋዴው በእግዚአብሔር አምኖ ወረቱን ሁሉ ከመዝገቡ አውጥቶ ይነግዳል ፤ ሁሉም በእግዚአብሔር ስም ስለሚያደርጉት እንደ ዓላማቸው እንደ ጀመሩትም ይፈጽሙታል ፤ መልካም ውጤትንም ያገኛሉ ።

ካህኑ ግን በበለጠ ለራሱም የሥራ ውጤትን ያገኘ ዘንድ ፣ ለሌላውም ያስተምር ዘንድ የጎላ የጸና ሃይማኖት እንዲኖረው ያስፈልጋል ፤ ስለዚህ የጸና ሃይማኖት የካህኑ የተለየ መታወቂያ ምልክቱ ይሆናል ።

፪ኛ/ ፍጹም ፍቅር በክርስቶስ ፡— ክርስቶስ በሰው ልጅ ላይ ያለውን ፍቅር ከከፍተኛ ዙፋኑ በመውረድ ፣ ከድንግል ማርያም በመወለድ ፣ ፍጹም ሰው ሆኖ በመታየት ገልጦታል ፤ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ወጣ ወረደ ፣ ሰው የሆነውን ሁሉ ሆነ ከኃጢአት በቀር ።

እንዲሁም ፍጹም ፍቅሩን ሕይወቱን በሞት በመለወጥ ገለጠው ፤ የሰውን ልጅ ለማዳን እርሱ ሞተ ፤ የእርሱን ሕይወት ለኛ ሰጠ ፤ የኛን ሞትም እርሱ ሙቶ እኛን አዳነን ።

የክርስቶስ ፍቅር በዚህ ዓይነት ሲገለጥ የክርስቶስ ተከታይ የሆነው ካህን ፤

፫/ በክርስቶስ ዘንድ ያለው ፍቅር ፍጹም መሆን አለበት ፤ ማለት በመከራ በችግር የማይለወጥ መሆን አለበት«ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ፣ ሞት ቢሆን ፣ ሕይወትም ቢሆን ፡ መላእክትም ቢሆኑ ፣ ያለው ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን ፣ ኃያላትም ቢሆኑ ፣ ከፍታም ቢሆን ፣ ዝቅታም ቢሆን ፤ ያለው ቢሆን ልዩ ፍጥረትም ቢሆን ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቻለሁ» (ሮሜ፡ ፰ ፡ ፴፱) ።

እንዲሁም ካህኑ በምእመናኑ የተወደደና ምእመናኑን የሚወድ ስለነርሱም ሕይወት የሚያስብ ፣ የሚናገር ፡ የሚሠራ መሆን አለበት ። እንዲያውም ከዚህ አልፎ መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርብ መሆን አለበት ፤ ካህኑ የምእመኑ እውነተኛ ጠባቂ ተከባካቢ እንደመሆኑ በምእመናኑ ላይ በሚደርስባቸው ችግር ሁሉ ተካፋይ መሆን እንዲያውም በእነርሱ እግር ገብቶ ታዳጊነቱን ማሳየት አለበት ።

እውነተኛ ጠባቂ ራሱን ለመንጋው አሳልፎ ይሰጣል ፤ ምንደኛው ግን በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ አውሬ ሲመጣ ባየ ጊዜ ጥሎ ይሸሻል ሲል ክርስቶስ በወንጌል ቃሉ አስረድቷል ፤ (ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፲፩—፲፫) ።



www.ethiopianorthodox.org

በመጀመሪያ አንድ ሰው ካህን የሚሆነው ክርስቶስ የሞተለትን መንጋ ለመጠበቅ ፡ ከሞትም ለማዳን ቀርጦ ሲገባ ነው ፤ እንዲህ ካልሆነማ ለምን ካህን ይሆናል !

ለራሱ ብቻ ክብርን ሲሻ ካህን የሚሆን ሰው ዓላማ ቢስ ነው ለማለት ይቻላል ።

ክርስቶስ በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን እንዲጠብቅ መንፈስ ቅዱስ ካህናትን የሁሉ መሪዎች አድርጎ አስነሣቸው፤ሾማቸው ፤ ስለዚህ ዛሬም ካህን የሚሆነው ሁሉ ይህን ዓላማ ተከትሎ የሚሠራ መሆን አለበት (የሐ ፡ ሥራ ፡ ፳ ፡ ፳፰) ።

ፍጹም ፍቅር የክርስቶስ ተከታይ ለመሆን የሐዋርያነትም አገልግሎት መታወቂያ ምልክት ነው ፤ እንግዲህ ይህ ምልክት የሌለው ሰው ካህን መሆን ቀርቶ ክርስቲያንነቱም ያጠራጥራል ማለት ነው ።

ካህን የሚሆን ፍጹም ፍቅር እንዲኖረው ማስፈለጉን ይኸም እውነተኛ መታወቂያ መሆኑን ክርስቶስ ሲያመለክት «አዲስ ትእዛዝ ሰጣችሁ እርስ በርሳችሁ ትፋቀሩ ዘንድ እኔ እንደ ወደድኳችሁ እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሁሉም ያውቃችኋል ሲል ተናግሯል (ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፴፬) ።

ፍቅር የሌለው ሰው ካህን መሆን ቀርቶ ክርስቲያንነቱ እንኳን ያጠራጥራል ፤ የክርስቶስ ተከታይ የሚሆነው በምንድን ነው ? በስም ወይም በልብስ ? እውነተኛው ካህን ክርስቶስን በግብር ይከተለዋል፤ ይመስለዋል፤ እውነተኛ ካህን መሆኑም በዚህ ይታወቃል ።

ክርስቶስ ቅዱስ ጴጥሮስን ሲሾመውና እንደገናም የሐዋርያነት ማዕርጉን ሲሰጠው የፍቅር ምልክት አይቶ ነው ፤ ማለት ሦስት ጊዜ ትወደኛለህ ? እያለ አዎን ሲለው በጎቼን፤ጠቦቶቼንም ፤ ግልገሎቼንም ጠብቅ እያለ ከፍቅሩ የተነሣ ጠባቂ እንዳደረገው እናውቃለን (ዮሐ ፡ ፳፩ ፡ ፲፭—፲፯) ።

ሌሎችንም ሐዋርያት እርሱ እንደወደዳቸው እስከ መጨረሻው እንዳፈቀራቸው ራሱ ጌታችን ገልጦ ተናግሮ እናገኘዋለን ፤ ስለዚህም ሐዋርያትን ጠባቂዎች አስተማሪዎች አደረጋቸው (ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፩) ።

ሥራው ሁሉ የሚፈጸመው በፍቅር ነው ፤ ባልንጀራችንን ከወደድነው ሀብቱን ሕይወቱን አናጠፋም ፤ ስሙንም አናጠፋም ፤ አደራውን እንጠብቃለን፤እንደዚህም ሁሉ ክርስቶስን ከወደድነው አካሉ የሚሆነው የምእመን ሕይወት ሲጠፋ ዝም አንልም ፤ የክርስቶስ ስም እንደጠፋ ያስቆጥራልና ። ክርስቶስን ከወደድን መንጋው ሲበተን ዝም አንልም ፤ እንዲሁም እርስ በርሳችንም ስንፋቀር ቤተ ክርስቲያናችን አትወድቅም ። ካህኑ ተልእኮውን ሊፈጽም የሚችለው እንከን የሌለበት ፍቅር በሰውም በእግዚአብሔርም ላይ ያለው እንደሆነ ነው ።



፫/ <u>ፈሪሃ እግዚአብሔር</u> ፡— ፈሪሃ እግዚአብሔር ለካህኑ ቀርቶ ለማንኛውም አማኒ አስፈላጊ ነው ፤ ማለት አምላክን እርሱ ፈርቶ አክብሮ ለሌላው የሚያስተምር የሚያሳምን ነውና ። ፈሪሃ እግዚአብሔር ስንልም እግዚአብሔር ይገድለኛል ያጠፋኛል በሚል ፍርሃት የሚፈራ ማለት አይደለም ፤ እግዚአብሔር አባታችን ስለሆነ ከበጎ አድራጊነቱ ፤ ከጸጋ ሰጭነቱ የተነሣ እናከብረዋለን ፤ ከውለታውም የተነሣ እንፈራዋለን ፤ እንዴት እርሱ ሲወደን እኛ እንጠላዋለን !

ጨካኝና ፈራጅ መሆኑን ዐውቀው የሚፈሩት ጠላትን ብቻ ነው ፤ ጠላት ምሕረትና ርኅራኄ የለውምና ። እንግዲህ እግዚአብሔርን በዚህ መልክ የምንፈራው ከሆነ ጠላቶቹ ነን ማለት ነው ፤ ግን እንዲህ አይደለም ሊሆንም አይገባም ። ከቸርነቱ ከምሕረቱና ከይቅር ባይነቱ የተነሣ አባታችን ብለን አባታችንም አድርገን እንቀበለዋለን እናከብረዋለን ፤ ሕጉን እንጠብቃለን ትእዛዙን እናከብራለን ።

ሁል ጊዜ የሚከብድ የወዳጅ ጥል ነው ፤ ስለዚህ የአባታችን የእግዚአብሔር ሕግ ማፍረስ ፤ እርሱንም ቸል ማለት ያሳዝናል ያስፈራል፤ ይኸን ካህኑ በሚገባ ያወቀ የጠበቀ መሆን አለበት ።

ፈሪሃ እግዚአብሔርን ገንዘብ ካደረገ ማንም ቢሆን አይበደልም ፤ ከሕጉ አይናወጥም ፤ በዋዛ በፈዛዛ ጊዜውን አያሳልፍም ፤ ግንኙነቱንም ከእግዚአብሔር ጋር አያቋርጥም ። በተለይ ካህኑ ፈሪሃ እግዚአብሔርን ገንዘብ ያደረገ እንደሆነ ሥራው ሁሉ ይከናወንለታል ፤ እንደ ዓላማው ተልእኮውን ለመፈጸም ይችላል ።

፬/ <u>መንፈሳዊ ቅንዓት</u> ፡— ካህኑ ለእግዚአብሔር አምልኮና ለሕጉ ለሥርዓቱም የሚቀና የሚቀረቀር መሆን አለበት ፤ በዚህም መለዮ ካህኑ መታወቅ መገመት አለበት ። ቅ/ሐዋርያት የክርስቶስ ውለታ ፤ የክርስቶስም ሥራ እየታሰባቸው መንፈሳዊ ቅንዓት እንደ እሳት እያቃጠላቸው በዓለም ተበትነው ያለይሉኝታ እየመሰከሩና እየሰበኩ ሕይወታቸውን አሳ



www.ethiopianorthodox.org

ለፉ ፤ ራሱ ክርስቶስ «ቅንዓተ ቤትከ በልዓኒ» ያለውን ቃል ተከትሎ ቤተ መቅደሱ በተሠራበትና በሚገባው አገልግሎት ሳያውል ባገኘው ጊዜ ሊታገስ አልቻለም ፤ ስለዚህ በውስጡ የሚሸጡትን የሚሸፍጡትንም ሁሉ ከቤተ መቅደስ አስወጣ ፤ ለአባቱ ቤት ለአባቱም ሕገጋት ቀናተኛ መሆኑን በሥራም በቃልም ገለጠ ።

አሁንም አንድ ካህን መንፈሳዊ ቅንዓት ከአለው ኩቶ አያመነታም ፤ ቸልም አይልም ሕገ እግዚአብሔርን ራሱ ጠብቆ ለሌሎች እንዲጠብቁ ያስደርጋል ። ምን ቸገረኝ በማለትና የምን ግዴ የሚሠራው መንፈሳዊ ቅንዓት የሌለው ካህን እንደሆነ ይታወቃል ፤ እንደዚህም ያለው ሁሉ የዕለት ጥቅሙንም ብቻ ይመለከታል ።

በዕለት ጥቅም የሚደለሉ እንስሳት ብቻ ናቸው ፤ ምክንያቱም እነርሱ የማሰብ የማመዛዘን ችሎታ የላቸውምና ፤ የዕለቱን በልተውና ጠጥተውም የማደር ፈቃድ ብቻ አላቸውና ።

ሰው ግን በተለይም ካህኑ ሁሉን አርቆ የሚመለከት መሆን አለበት፤ እንዲያውም የዚህን ዓለም ብቻ ሳይሆን የወዲያኛውን ዓለም ተስፋ የሚያደርግ ስለሆነ የሚያስበው ፥ የሚናገረው ፥ የሚሠራው በዚህም ዓለም በወዲያኛውም ዓለም ለሚሆነው ነውና ።

፫/ ንጽሕና ፡ ቅድስና ፡—የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነ ካህን ከሁሉ በበለጠ ንጽሕናን ቅድስናን ገንዘብ ያደረገ መሆን አለበት፤ምክንያቱም፡—

፩ኛ/ ካህኑ እግዚአብሔርን የሚያገለግል ስለሆነ ከእርሱ ለመቅረብ የሚችል ተልእኮውንም የሚፈጽም ንጹሕ ቅዱስ የሆነ ነውና ።

፪ኛ/ ሕዝቡን የሚያነጻ የሚቀድስ ነውና ፥ አስቀድሞ እርሱ ንጹሕ ቅዱስ መሆን አለበትና ።

ካህኑ ከተልእኮው አንደኛው በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ሕዝቡን ማንጻት መቀደስ ነው ፤ ታዲያ ሌላውን የሚያነጻውና የሚቀድሰው ካህን እርሱ ካልነጻ እንዴት ሌላውን ሊያነጻ ይችላል? እንዲያውም የበለጠ እንዳያሳድፍ ያሰጋል ። ሌላውን በደል ሁሉ ካህን ይቅር ሲል ይቅርታም ሲያደርግ የክህነት ማዕርግ ግን ከአደፈ ከተጓደፈ በኋላ ይቅርታ የሌለው በመሆኑ አስቀድሞ በንጽሕና ለመያዝ ትልቅ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ።



ቅዱስ እግዚአብሔር በቅድስናው ለዘለዓለም የሚኖር ነው ፤ ስለ ዚህ የሰው ልጅ ሁሉ ቅዱስ ይሆን ዘንድ «ኩኑ ቅዱሳነ እስመ አነሂ ቅዱስ «ሲል በብሉይ ኪዳን አዟል (ዘሌዋ ፥ ፲፩ ፥ ፵፬) ። ቅዱስ ጴጥሮስም ክርስቲያኑ ሕዝብ ሁሉ በንጽሕና መኖርምንጽሕናን ገንዘብ ማድረግ ተገቢ መሆኑን በመግለጥ ይኸንኑ ትምህርት በመድገም ተናግሯል (፩፥ ጴጥ.፩. ፲፮) ።

ቅድስና የካህኑ የተለየና ከሁሉም የበለጠ መታወቂያ መመዘኛም መገመቻም ነው ። ሥልጣነ ክህነት የተዋሐደው ፥ የማሠር የመፍታት ኃይል እንዳለው የሚታወቅበት ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት ፥ የሚታይበት ፥ ንጽሕናው ቅድስናው እንደሆነ መድኃኒታችን ኢየሱስ «ብፁዓን ንጹሐን እስመ እሙንቱ ይሬእይዎ ለእግዚአብሔር» ሲል አስረድቷል (ማቴ ፥ ፭ ፥ ፲) ።

ይኸንንም መሠረት አድርጎ አባ ሕርያቆስ «እስመ በአንጽሖ መንንፈስ ርእይዎ ነቢያት ለእግዚአሙ» ሲል ተናግሯል ፤ (ቅዳሴ ማርያም) ።

ካህኑ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርበው ሌላውንም ምእመን ሊያቀርበው የሚችል ንጽሕና ቅድስና ያለው እንደሆነ ነው ፤ ክህነታዊ ተልእኮውን ሁሉ የሚያከናውነው ንጽሕናን ቅድስናን ገንዘብ ያደረግ እንደሆነ ነው ፤ ያለዚያ ክንፉን እንደተሰበረ መብረርም እንደሚሳነው አሞራ ተግባሩን ሁሉ ለማከናወንና ግዳጁን ለመፈጸም የማይችል ሆኖ ይኖራል ።

፬/ ፍጹም ዕውቀት ፡— ምንም ከሰው ወገን ሙሉና ፍጹም ዐዋቂ ባይኖር ካህኑ ከማንኛውም ሰው የተለየና የተሻለ ዕውቀት ሊኖረው በግድ ያስፈልጋል ፤ ምክንያቱም ሁሉንም የሚመክር ፥ ሁሉንም የሚያስተምር ነውና ።

እንዲያውም የካህን ዕውቀት እጥፍና ድርብ መሆን አለበት ፤ ማለት ማንኛውም ሰው የሚያውቀውን ሁሉ ሰው እንደመሆኑ ከሰው ጋርም እንደመኖሩ ማወቅ ግድ አለበት ፤ ያለዚያ ከማኅበሩ ይለያል ፤ ከሰው ተራ ይወጣል ፤ ከዚህ በተለይ ግን ፤

ሀ/ የተለየ ዕውቀት ፥ —ለካህኑ የተለየ ዕውቀት ያስፈልገዋል ፤ ይኸውም ቴዎሎጂ የተባለው ጥናት ነው ። ለካህኑ ተገቢ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ሳያውቅ ፥ በእነርሱም ሳይጸና ካህን መሆን የለበትም ። ዓላማውን ሳያውቅ ለምንም እንደ ተሠለፈ ምንም ማድረግ እንዳለበት ሥራውም ምን ዓይነት እንደሆነ ሳያውቅ የተሰለፈ ከሆነ በምንም መልክ ተል



www.ethiopianorthodox.org

እኮውን ሊፈጽም አይችልም ። እንግዲህ ለራሱ የማያውቅ ለሰው ምን ሊያደርግ ይችላል ተብሎ እምነት ይጣልበታል ! እንዴትስ በኃላፊነት ቦታ ይቀመጣል ! ስለዚህ ካህኑ የተለየ ዕውቀት የተለየም ትምህርት በግድ ያስፈልገዋል ።

ካህንም የሚባለው ካህንም የሚያሰኘው የካህኑን ሞያ በመያዙ በካህኑ ቦታ በመገኘቱ ነው እንጂ በምእመንነት እያለ ካህን ሊሆን ወይም ሊባል አይችልም ፤ እንዲህስ ከሆነ እንዴት አድርጎ ሌላውን ሊመራ ይችላል !

እንግዲያውስ «ዕውሩን ዕውር ቢመራ ገደል ይገባል ሁሉም በየተራ» እንደተባለው ሁሉም ከድኅነት ውጭ ይሆናሉ ።

ስለዚህ ካህን የሆነ ሁሉ የተወሰኑትን የትምህርት ዓይነቶች ሁሉ ጠንቅቆና አጠቃሎ መማርና ማወቅ አለበት ።

ለ/ ጠቅላላ ዕውቀት፤ — ዘመኑ የሳይንስ ዘመን እንደመሆኑ ካህኑ ተጠያቂ እንጂ ጠያቂ ሆኖ እንዳይገኝ ዘመኑ ያፈራውንም ዕውቀት ሁሉ በመጠኑም ቢሆን ያወቀ መሆን አለበት ።

ሰው በዕውቀት ኃያላኑን አራዊትንና እንስሳትን ይገዛል ፤ ይኸም የተፈጥሮ ዕውቀቱ ነው፤ በበለጠ በትምህርት ዕውቀት የተራቀቀ ከሆነ ሰውን ይገዛል፤ሰውን እጅ ያደርጋል ፤ ያለዚያ እርሱም ይማረካል ፤ ለሌላ አድማቂ የሌላም ተላላኪ ይሆናል ፤ ስለዚህ ካህኑ ዕድሜውን ሙሉ ሲማር መኖር አለበት ።

እነዚህ ነገሮች በካህኑ ጉልተው ሊታዩ መታወቂያውም ፣ መለያውም ሊሆኑ ይገባል ።

እነዚህ መታወቂያዎች ካሉት እርሱም ሳይፈራ ሳያፍር ተግባሩን ሊያከናውን ይችላል ፤ ምእመናኑም በሁኔታው አምነው ቃሉን ይሰማሉ ፤ ትእዛዙን ይከተላሉ ፤ እውነተኛ አባት አድርገው ይይዙታል እግዚአብሔርም የሥራው ሁሉ ረዳት ይሆነዋል ፤ ስለዚህ እንደ ዓላማው ተግባሩን በመፈጸሙ ተደስቶ ይኖራል ።

የካህኑ ሀብት የካህኑም የደስታ ሕይወት የሚሆነው የገባበትን ግዴታ መወጣትና የሥራውም ሁሉ መቃናት ነውና ። እንግዲህ ካህኑ ምን መሆን እንዳለበት ካህን የሚባለው የትኛው እንደሆነ መለያው ምን እንደሆነ ተረዳን ።



# ክፍል ፪ ሥርዓተ አምልኮ

የምእመናን ጠባቂ (አበ ነፍስ) የሚሆነው ካህኑ የመጀመሪያ ተግባሩ በጸሎት ጽሙድ መሆን ፤ ለቅዱስ አምላክ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ፣ ለምእመናን ሕይወት ሰላምና ጤንነት ምልጃ ፤ ስእለትና፤አስተብቍዖት ማድረግ ነው ። ይኸንንም ተግባር ጊዜና ሰዓት ጠብቆ ማቅረብ መፈጸም ዋና የካህኑ ተልእኮ ነው ።

ቅዱስ ጳውሎስ ተወዳጅ ደቀ መዝሙሩን ጢሞቴዎስን ለኤፌሶን ሀገረ ስብከት ጠባቂ (አበ ነፍስ)አድርጎ ሲልከው ከሁሉ በፊት ጸሎት ፣ ስእለትና አስተብቍዖት፣ ምልጃም እንዲያደርግ ከፍተኛ ማስጠንቀቂያን ሰጥቶ ነው ። እርሱንም እንዲሁ ሲል ይገልጠዋል ፤ «እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰል በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር ልመናና ጸሎት ፣ ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ» እንዲደረግ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ - - - (፩ ጢሞ ፣ ፪ ፣ ፩—፬) ።

አምልኮተ እግዚአብሔር ስንልም ብዙ መልክ ያለውና በብዙ መልክ የሚፈጸም ስለሆነ ካህኑ ግዴታው መሆኑን ዐውቆ ተግቶ ነቅቶም መፈጸም አለበት ፤ አምልኮተ እግዚአብሔር በመጠኑም ቢሆን በጸሎት ፤ በምጽዋት ፣ በስግደት ፣ በጾም ፣ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንንም በመፈጸምና ይኸን በመሳሰለው ሁሉ ይፈጸማል ። እንግዲህ እነዚህ እያንዳንዳቸው እንዴት እንደሚፈጽሙ በሚከተለው መልክ እንዘረዝራለን ።

ሀ/ ጸሎት፡— ጸሎት ራሱ በ፫ ይከፈላል ፤

፩/ ምስጋና፡— ምስጋናም ማለት አምላክ አማልክቱን ፣ ንጉሠ ነገሥቱን እግዚአብሔርን በማንኛውም ጊዜ ፤ በማንኛውም ምክንያት ያለማቋረጥ ማመስገን ነው ። ሰው የተፈጠረው ለምስጋና ስለሆነ ሰው ሁሉ ትንሹም ትልቁም እንደ የችሎታው ለአምላክ ምስጋና ማቅረብ ፣ ተገዥነቱንም መግለጥ ግድ አለበት ፤ ለዚህም አብነት የሚሆነው ካህኑ ስለሆነ ፣

፩ኛ/በአስተማሪነቱ ፣ ፪ኛ/ በግሉ ለራሱ ጸሎት ማድረግ አለበት ፤ መጀመሪያውም ተልእኮው ይኸው ነው ።

ማንኛውም ሰው ቢያዝንም ቢደሰትም፤ መንገድ ቢሄድም፤ ቢቀመጥም፤ አምላኩ ምስጋና ማቅረብ አለበት ፤ በተለይም የሕዝብ ጠባቂ የሆነው ካህኑ እንደመላእክት ለእግዚአብሔር ምስጋና ሁል ጊዜ ማቅረብ አለበት ።



www.ethiopianorthodox.org

ካህኑ ከሕዝበ የሚለይበት ፥ የሚታወቅበትም ጸሎተኛነቱ ፥ በጸሎት ከእ
ግዚአብሔር ጋር መገናኘቱ ነው ፤ ምክንያቱም ተልእኮው ለዓለማዊ ግብር
ሳይሆን ለመንፈሳዊ ተግባር ነውና ። ጸሎትም ሲያደርግ በመጀመሪያ ለእግ
ዚአብሔር ምስጋና በማቅረብ ፥ ውለታውን በመናገር መጀመር አለበት ።

ጌታችን ኢየሱስ ጸሎት በአስተማረ ጊዜ በመጀመሪያ ምስጋና
ማቅረብ እንደሚገባ እንዲህ ሲል አስተምሯል «አባታችን ሆይ በሰ
ማያት የምትኖር ፥ ስምህ ይቀደስ ፥ መንግሥትህ ትምጣ ፥ ፈቃ ድህ በሰ
ማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን» (ማቴ ፥ ፮ ፥ ፱—፲ ።

እንግዲህ እኛም የእርሱን ፍለጋ የተከተልን በየጊዜው ንጹሕ ምስ
ጋና ለአምላካችን ማቅረብ አለብን ። የሕዝቡ ጠባቂ የሆነው ካህኑ ይቅርና
ማንኛውም ሰው በደስታም ላይ የሆነ፤ማለት በጫጉላ ያለ ሙሽራም ቢሆን፤
በኃዘንም ላይ ያለ ሰው ቢሆን ፥ በኀዘን በችግርም ያለ ቢሆን፤ለምሳሌ በግ
ዞትም በእሥራትም ላይ ያለ ቢሆን፤ሰው የተፈጠረው ለምስጋና መሆኑን
ዐውቆ አምላኩን ያመሰግን ዘንድ ግዴታ አለበት ። ንባብና
አእምሮ ያለው ሰው ቀርቶ ሌላው ግዑዝ ፍጥረት የሆነው ሁሉ ለእግዚአ
አብሔር ምስጋና እንዲያቀርብ ቅ-መጽሐፍ ይናገራል (መዝ ፥ ፲፱ ፥ ፩)።

፪/ልመና፥--ሁለተኛው የጸሎት ክፍል ምልጃ ፥ ልመና ነው ። ይኸም
መጀመሪያ ስለራስ ፥ ቀጥሎ ስለ ሕዝቡ (ስለሚጠብቃቸው) በአጠቃላይም
ስለ ዓለም ሰላም ሁሉ መለመን አለበት ፤ ግዴታ ተግባሩም ነው ። የእግዚ
አብሔር ወኪል የሆነው ካህኑ ከምልጃ ከልመና ፥ ከጸሎት ወደኋላ ማለት
ከቶ የለበትም ፤ ከእርሱ ጸሎትና ምልጃ የተነሣ አምላክ ለሕዝ ቡ ይቅርታ
ውን ለማድረግ ፈቃደኛ ነውና ። «ለምኑ ይሰጣችኋል ፤ እሹ ታገኛላችሁ
ደጅ ምቱ ይከፈትላችኋል» ሲል የተናገረ አምላክ እውነተኛ ስለሆነ ከእ
ርሱ ስለማይቀር የለመነውን እናገኝ ዘንድ ልመናችንን በሰፊው ማቅረብ
አለብን (ማቴ ፥ ፯ ፥ ፯) ።

እኛ ከቸልተኝነታችን የተነሣ ጸሎት ባለማድረጋችን ከአልቀረብን
በቀር ከአምላክ ዘንድ አንድም የሚቀርብን ነገር የለም ፥ ስለዚህ ሁሉን
የሚያውቅና እኛ የምናውቅበትን አእምሮ ፤ የምንሰማበትን ጆሮ የፈጠረ
አምላክ ልመናችንን ሰምቶ ሁሉንም ዐውቆ ፤ የጠየቅነውን ሁሉ ይፈጽም
ልናል ።

ልመና ማቅረብ እንደሚገባን ከጸሎታችን ውስጥ ፪ኛው ክፍል
ልመና መሆን እንደሚገባ ክርስቶስ አስተምሯል ፤ እርሱም እንዲህ ይላል
«የዕለት እንጀራችንን ስጠን ለዛሬ ፥ በደላችንንም ይቅር እንድትለን



እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል ወደፈተናም አታግባን ከክፉ አድ
ነን እንጂ» ጌታ የልመናውን መልክ በዚህ ለይቶ አመልክቶ እናገኘዋለን
(ማቴ ፥ ፮ ፥ ፲፱—፲፩ )።

በዚህ መልክ ለተለያዩ ሰዎች ፤ ስለተለያዩ ችግሮች መለመን ይቻላል ።
በተለይ ግን ሁል ጊዜ ስለ ሰው ልጅ ደኅንነት ፥ ስለዓለም ሰላም መለመን
የካህኑ ተልእኮ ነው ። ይኸም ለሰው ልጅ ሁሉ ተገቢ ሲሆን ካህኑ በበ
ለጠ ስለ ራሱም ፥ ስለቤተሰቡም ፥ ስለምእመናኑም ፥ ስለ ሀገሩና በጠቅላ
ላው ስለ ኅብረተሰቡ ሁሉ ምልጃ ፤ ስእለትና አስተብቊዖት ማድረግ
ግዴታው ይሆናል ።

እንግዲህ ካህኑ በዚህ መልክ በጸሎት ጽሙድ እየሆነ ሌላውም እን
ዲህ እንዲሆን ማስተማርና መምከር ግዴታው ነው ። እርሱም ራሱ ንጹሕ
የሚሆነው ፥ የሌላውንም በደል የሚያነጻው በስእለትና በአስተበቊዖት
በምልጃም በጠቅላላም በጸሎት ተልእኮውን የፈጸመ እንደሆነ ነው ።

ጸሎት የካህኑ የተለየ ቀዳሚ ተግባሩ ነው ፤ በዚህም ምክንያት ሁል
ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ያልተቋረጠ ግንኙነት ይኖረዋል ፤ ጸሎት የሰውና
የእግዚአብሔር ግንኙነት መግለጫ ወይም ውይይት ነው ። ሰው እግዚአ
ብሔርን በጸሎት ይጠራዋል ፤ ችግሩን ገልጦ ይነግረዋል ፤ ዋይታውን
ያካፍለዋል ፤ እግዚአብሔር ደግሞ ጩኸቱን ይሰማዋል ፤ ጸሎቱን ይቀበ
ለዋል ፤ ስለዚህ ፥ ይረዳዋል ፥ ግዳጁንም ይፈጽምለታል ።

፫/ ምስጋና (መደምደሚያ) ፥—እንደገና እግዚአብሔርን ስለ ውለ
ታውና ስለበጎ አድራጎቱ ያመሰግናል ፤ ምክንያቱም የለመኑትን የማይነሳ
የነገሩትን የማይረሳ ፥ ዝቅተኛም ነው ብሎ ማንንም ሰው ቸል የማይል አም
ላክ እውነተኛ አባት ነውና ።

እግዚአብሔር ኃያልና ገናና ሲሆን ግንኙነቱን ከደካማው ከሰው
ጋር ያደረገው ስለ ቸርነቱ ነው ፤ ግን የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ኃይል
በመግለጥ ፥ ገዥነቱንና አስተዳዳሪነቱን በመመስከር ምስጋና ያቀርብለ
ታል፤ይኸንንም ጌታ ራሱ ሲያስተምር «መንግሥት ያንተናትና፤ኃይልም፥
ምስጋናም ለዘለዓለሙ አሜን»ሲል ገልጦ አስተምሯል(ማቴ፥ ፮ ፥ ፲፫) ።

በዚህ መልክ የተዘጋጀ ወይም ይኸን የመሰለ ጥንታዊም አዲስም
የጸሎት ሥነ ሥርዓት ይዞ (ተከትሎ) ካህን ሁልጊዜ መጸለይ አለበት፤ሕዝ
ቡንም ማስተማር አለበት ። ሕዝቡን ለማንጻት ፥ ለማጽናት ከክፉ ነገርም
ሁሉ ለመጠበቅ ካህኑ በምንም መልክ የማያቋርጥ ጸሎት መጸለይ አለበት።



www.ethiopianorthodox.org

ማንም ሰው ሳይታክትና ሳይሰለች ሳያቋርጥም መጸለይ እንዳለበት ጌታ ሲያስተምር በመበለቲቱና በጨካኙ ፈራጅ መስሎ ተናግሯል(ሉቃ፲፰. ፩—፲። ) እንግዲህ ከላይ በተገለጸው የጸሎት ሥነ ሥርዓት ዓይነት በተለ ያዩ ሰዓቶች ማንኛውም ሰው መጸለይ እንዳለበት ተናግረናል ፤ በተለይ ግን ካህኑ ሕይወቱ በጠቅላላው ከጸሎት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ሁል ጊዜ በጸሎት ጽሙድ መሆን አለበት ።

ከአምልኮት ሥርዓት ውስጥ የሚገቡ በእርሱም አማካይነት ጸሎትና ስእለት አስተብቍዖትም የሚፈጸምባቸው ፤ ጸጋ ፣ በረከት ፣ ልጅነት ፣ የሚሰጥባቸው ፣ ድኅነተ ሥጋና ድኅነተ ነፍስ የሚገኝባቸው ፯ቱ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ተብለው የሚጠሩት ናቸው ።

ካህኑ እነዚህን በየጊዜው ሲፈጽም የጠባቂነቱ ቀንበር ኃፊነቱም ይወገድለታል ። እነዚህም ምሥጢራት ሲፈጸሙ የተለየ ጸሎት፤ ምስጋና ፤ ምልጃም ይደረጋል ፤ በዚህን ጊዜ ካህኑ ለጸሎት ጽሙድ መሆኑን ይገልጣል።

በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንም አፈጻጸም በዕድሜ ፤ በጾታ ፤ በማዕርግ የተለያዩትን ወገኖች ሁሉ ካህኑ ያገኛቸዋል ። በተለያየም መልክ እያንዳንዱ የሰው ልጅ እነዚህን ምሥጢራት ይፈልጋቸዋል ፤ እንግዲህ ካህኑም እነዚህን ለመፈጸም ተገቢ ሆኖ መቅረብ አለበት ፣ ምእመናኑም ይኸን ለመቀበል ተገቢ ሆነው መቅረብ አለባቸው የጋራ ችግራቸውም በዚህን ጊዜ ተወገደላቸው ።

## ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ፤

በአምልኮት ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዘው የሚገኙት ፤ ካህኑም ተልእኮውን በትክክል የሚፈጽምባቸው ፣ ኃላፊነቱን የሚወጣባቸው ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እየተባሉ የሚጠሩ ናቸው ።

ሕዝቡን ለማንጻት በእምነቱና በትምህርቱ ፣ በሥነ ሥርዓቱም ለማጽናት ፤ አምልኮተ እግዚአብሔርንም በሚገባ ለመፈጸም እነዚህ ምሥጢራት በየጊዜው መፈጸም አለባቸው ።

እንዲሁም እያንዳንዱ አማኒ እምነቱን የሚገልጥባቸው ፣ ከኃጢአት የሚነጻባቸው ፤ በእምነቱ ጸንቶ ለመኖር የሚያስችሉት እነዚህ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ናቸው ።
እነዚህም ምሥጢራት ለሰው ሁሉ የሚታደሉ ናቸው ብንልም ምሥጢር እንደመሆናቸው መጠበቅ በጥንቃቄም መያዝ አለባቸው ፤ ላልመሰሉና ላላመኑ አይሰጡምና ፤ በእምነት እንኳን መስለው በሥነ ምግባራቸው የተለዩ ከሆነ የማይሰጡ ናቸው ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አክብራ የምትቀበላቸው ፯ቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚከተሉት ናቸው ።

፩/ ምሥጢረ ጥምቀት
፪/ » ሜሮን
፫/ » ቊርባን
፬/ » ንስሐ
፭/ » ክህነት
፮/ » ተክሊል
፯/ » ቀንዲል ናቸው ።

እነዚህም ፯ቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሰው ልጅ ሃይማኖታዊና ሥነ ምግባራዊ ሕይወቱ የሚደገፍባቸው ናቸው ። እንዲሁም የሰው ልጅነቱ የሚታደስባቸው ፤ ፍጹም መንፈሳዊ ለውጥ የሚያገኝባቸው ማእከሎች እነዚህ ምሥጢራት ናቸው ።

እነዚህ ምሥጢራት በቤተ ክርስቲያን መዝገብነት የሚጠበቁ ሲሆኑ ቤተ ክርስቲያንም በኃጢአት የወደቁትን ታነሣበታለች ፤ የታሠሩበትን ትፈታበታለች በጠቅላላውም ለሰው ልጅ መንፈሳዊ ኃይልን የምትሰጥባቸው የምታስተላልፍባቸውምናቸው።
ክነዚህም ምሥጢራት አንዱ ከሌላው ሊለይ አይችልም ፤ ፍጹም ድኅነትን ለማግኘት ሁሉንም መፈጸም በግድ ያስፈልጋል ፤ አንዱ ከሌላው ተለይቶ ከተጓደለ ሙሉ መንፈሳዊ ሕይወት ሊገኝ አይችልም፤ ቤተ ክርስቲያንም እያንዳንዳቸውን ምሥጢራት በተለያዩ ጊዜያቶች ለተለያዩ ሰዎች ትፈጽመው እንጂ ፯ቱ ሁሉ መጠበቅ ፣ መፈጸምም በግድ አለባቸው ። ከ፯ቱ ምሥጢራት ውስጥ ፬ቱ በግድ ለሰው ልጅ ሁሉ ያስፈልጋሉ ፤ ማለት ልጅ ነው ትልቅ ነው ፤ ወንድ ነው ሴት ናት ፣ ካህን ነው ፣ የጨዋ ልጅ ነው ሳይባል ለሁሉም በግድ ያስፈልጋሉ ፣ እነርሱም ጥምቀት፣ ሜሮን፣ ቊርባን ፣ ንስሐ ናቸው ።

ማንኛውም ሰው ከሥላሴ ለመወለድ ፣ በዘርም ከወረደው ኃጢአት ለመንጻት ፣ ከብልየትም ለመታደስ በግድ ጥምቀት ያስፈልጋል ።

ከጥምቀትም ቀጥሎ ልጅነቱን ለማጽደቅ ፣ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ማኅተመ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ሜሮን ይቀባል ። ማንም ቢሆን ጥምቀትን ተጠምቆ ሜሮን ወዲያው መቀባት አለበት ።





www.ethiopianorthodox.org

ጥምቀት መወለድ ፥ ሜሮን ደግሞ መንፈስ ቅዱስን መቀበል ልጅነትን ማረጋገጥ ነው ። የተወለደው ሰው ምግብ ያስፈልገዋል ፤ ስለዚህ ወዲያው ሥጋውንና ደሙን ይቀበላል ፥ ማለት መንፈሳዊ ምግብን ይበላል ፤ መንፈሳዊ መጠጥንም ይጠጣል ። እንዲሁም የተወለደው ሰው በየጊዜው መታጠብ መንጻት ስላለበት ንስሓ ይገባል ፤ ከበደሉም ይነጻል፤ ስለዚህ በየጊዜው ንስሓ መግባት አለበት ።

እነዚህ ፬ቱ ምሥጢራት በዚህ መልክ በአንድ ጊዜ ይፈጸማሉ ፤ ፩ኛው ከሌላው ተለይቶ ሊቀር አይችልም ።

ሌሎቹ ፫ቱ ምጢራት ግን ክህነት ፥ ተክሊል ፥ ቀንዲል የተባሉት ለተወሰኑ ራሳቸውንም ለዚህ ላበቁ እግዚአብሔርም ለወደደላቸው ሰዎች ብቻ እንጂ ለሁሉ አይሰጡም ። ሁሉ ካህን ሊሆን አይችልምና ፥ ከፍ ያለ መመዘኛ ሊኖር ይችላል፤ ያንን ማለፍ በግድ ያስፈልጋልና ። ከዚህም በቀር በጾታ የሴት ወገን ካህን አይሆንምና። እንዲሁም ሁሉም ሊያገባ አይችልም ጃንደረባ ሆነው የሚወለዱ አሉና ፥ ሰው ጃንደረባ ያደረጋቸውም አሉና ፥ ራሳቸውንም ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ፥ ስለ ወንጌል ትምህርትም ሲሉ ጃንደረባ ያደረጉ ይገኛሉና (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪ ።)

ከነዚህም ምክንያቶች በቀር ቤተሰብን የማስተዳደር ችሎታ ፥ ሥራን የመሥራት ፈቃድና የመውጣትም የመውረድም ኃይልን ይጠይቃልና ። ሚስት አግብቶ ቤተሰብን መሥርቶ እንዲሁ መተው ተገቢ አይደለምና ፥ የሚያገቡ ሁሉ ይኸን መቻል አለመቻላቸውን ማመዛዘን በግድ ስላለባቸው ሁሉም ሊያገባ አይችልም ።

ሰው ሁሉ ሊታመም ስለማይችል ጸሎተ ቀንዲልም ለሁሉ አይፈጸምም ፥ በመንፈስ ወይም በሥጋ ደዌ አድሮባቸው ፤ በሽታ ጸንቶባቸው ጸሎተ ቀንዲል እንዲፈጸምላቸው ከጠየቁ በቀር ለሰው ሁሉ እንዲሁ አይፈጸምምና ።

ከነዚህ ከ፯ቱ ምሥጢራት ውስጥ በየጊዜው እየተደጋገሙ የሚፈጸሙ አንድ ጊዜም ብቻ የሚፈጸም አለ ፤ አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸሙ ግን በምንም መልክ የማይደገሙ ናቸው ።

እነርሱም ፡—ጥምቀት ፥ ሜሮን ፥ ክህነት ናቸው ። ጥምቀት አንዲት ናት፥ «ነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለስርየተ ኃጢአት» ሲሉ ፫፻፲፰ ሊቃውንት ወስነዋል ።

ቅዱስ ጳውሎስም «አንድ ጌታ አንዲት ሃይማኖት ፥ አንዲት ጥምቀት» እያለ የጥምቀት አንድነቷን ገልጾ ጽፎአል (ኤፌሶ ፡ ፬ ፡ ፭) ።



አንድ ጊዜ ከተጠመቁ በኋላ ጥምቀት በምንም መልክ አይደገምም ፤ ፍጹም በደል በድሎ እንኳን ቢገኝ ንስሓ ይገባል እንጂ እንደገና አይጠመቅም። ያመነ የተጠመቀ ሁኖ ሳለ ከሃይማኖት ውጭ ሆኖ ቆይቶ ቢመለስም እንኳን ንስሓ ይሰጠዋል እንጂ እንደገና አይጠመቅም ።

ሜሮንም ከጥምቀት ጋር የሚሄድ የልጅነቱ ማጽደቂያ ፤ የመንፈስ ቅዱስ መሰጠት ማረጋገጫ በመሆኑ ወዲያው ከጥምቀት ጋር እንደተሰጠ እርሱው በቂ ነው አይደገምም ።

ክህነትም በዲቁና ፥ በቅስና ፥ በጵጵስና አንድ ጊዜ ከተሾመ በኋላ በዚያው ሥልጣን ላይ አይደገምም ፤ ከዲቁና ወደ ቅስና ፥ ከቅስናም ወደ ጵጵስና ይራመዳል እንጂ በምንም መልክ ቢሆን በዚያው ማዕርግ ላይ አይደገምም ። በአንድ ማዕርግ ላይ ተደግሞ ከተገኘ ሰጭውም ተቀባዩም እንደሚቀጡ የቤተ ክርስቲያን ሕግ ያስረዳል ።

ተክሊል (ጋብቻ) ደግሞ ከሚደጋገሙትም ከማይደጋገሙትም ምሥጢራት ገብቶ ይቈጠራል ።

ከማይደገሙት ምሥጢራት ገብቶ የሚቈጠርበት አንድ ጊዜ ከተጋቡ በኋላ በምንም መልክ መፋታት ፈጽሞ ክልክል ነውና።በነውር ከተፋቱ በኋላ ደግሞ ማግባት በቤተ ክርስቲያን ዘንድ የተከለከለ ነውና ፥ ቤተ ክርስቲያናችንም የምትቀበለው የአንድ ጊዜን ጋብቻ ነውና ።

ከሚደገሙ ምሥጢራት ጋብቻ መግባቱ ከሁለቱ ጾታዎች መካከል ፩ኛው በሞት የተለየ እንደሆነ በሕይወት ያለው የማግባት ፈቃድን ያገኛል፤ እንዲሁም ከባልና ከሚስቱ ፩ኛው የጋብቻውን እምነት ያጎደለ ፥ በደል የበደለ እንደሆነ ፤ የሥነ ምግባር ጉድለት ስላደረገ እርሱ እንደሞተ ተቈጥሮ ላልበደለው ወገን የማግባት ፈቃድ ይሰጣልና ።

እየተመላለሱ ሁልጊዜ ሲደገሙ የሚኖሩ ምሥጢራት ደግሞ ፫ ናቸው ፤

እነርሱም ፩ኛ ቍርባን ነው ፤ እሱም በየዕለቱ ወይም በየሳምንቱ ፥ ወይም በየወሩ መቍረብ ተገቢ ነውና ። እንዲያውም በዓመት ፫ ጊዜ ያህል እንኳን የማይቆርብ ክርስቲያን ነው ሊባል የማይገባው ነው ፤ ስለዚህ ማንኛውም ክርስቲያን ሁል ጊዜ ሲቈርብ መኖር አለበት ።

፪ኛ/ ንስሐ ፤ በየዕለቱ ንስሐ መግባት ለክርስቲያን ሁሉ በጣም አስፈላጊ ነው ፤ የሰው ልጅ ሕይወት አንድ ቀን እንኳን ቢሆን ሳይበድል የሚውል የለምና ፥ እንዲያውም ከተቻለ በጥዋትም በማታም መናዘዝና ንስሐም መግባት ለክርስቲያን ሁሉ በጣም አስፈላጊ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ለሌላው ምሥጢር ሁሉ ተገቢ ሆኖ ለመቅረብ እንዲችል አንድ ክርስቲያን ሁል ጊዜ ንስሐ መግባት በግድ አለበት። በደሉን ተሸክሞ፤ከምሥጢራት ሁሉ ርቆ የሚኖረው ሰው ሁሉ ክርስቲያን ሊባል ከቶ አይቻልም፤ ስለዚህ ንስሐ እየተደጋገመ ሊፈጸም ይችላል ።

፫ኛ/ ቀንዲል ፤ ቀንዲል የተባለው ምሥጢር ለኃጢአት ስርየትን የሚሰጥ ፣ ለበሽታም ፈውስን የሚያድል በመሆኑ በየጊዜው እየተደጋገመ ይፈጸማል ።

ምሥጢራት ሁሉ ይህንን የመሰለ መልክ ስላላቸው ክርስቲያኑ ሁሉ በየመልካቸው እንደአስፈላጊነታቸው በየጊዜው ሊፈጽማቸው ይገባል ።

## ምዕራፍ ፩/ ምሥጢረ ጥምቀት ፣

ሀ/ የቃሉ ትርጒም ፣ ጥምቀት ማለት መነከር ፣ መዘፈቅ ፣ መጥለቅ ፣ ማለት ነው ፤ በተጠመቅን ጊዜ በማጥመቂያው ቦታ በተባረከው ውኃ ፫ ጊዜ ጥልም ፣ ብቅ እያልን እንጠመቃለንና። ካህኑ ውኃውን በገንዳ አድርጎ የጥምቀቱን ጸሎት ይጸልያል ፤ ይባርከዋል ፤ ያከብረዋል ፤ በዚህ ጊዜ ውኃው ከጌታ ጐን በዕለተ ዐርብ የፈሰሰውን ውኃ ይሆናል ። ከዚህ በኋላ አጠምቀከ በስመ አብ ፣ አጠምቀከ በስመ ወልድ ፣ አጠምቀከ በስመ መንፈስ ቅዱስ ይኩን ስምከ - - -» እያለ ፫ጊዜ እየነከረ ያወጣዋል፤ ይኸ ጥምቀት ይባላል ፤ በውኃው መነከሩ ወደ መቃብር መግባቱን ፣ ከውኃው መውጣቱ ደግሞ የትንሣኤውን ምልክት ይሰጠናል ። ይኸን እየመላለሰ ፫ ጊዜ ማድረጉ በሥላሴ የማመኑ ምሳሌ ፣ ቃሉ ሳይለወጥ ፩ መሆኑ የአንድነት ምሳሌ ነው ።

ጥምቀት የመቃብር ምሳሌ መሆኑን ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያስተምረናል« ወይስ አታውቁምን እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቅን በሞት እንደተጠመቅን ፣ እንዲህ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን በሞት፣ ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሣ በአብ ክብር እንዲሁም እኛ ደግሞ በአዲስ ሕይወት እንሄድ ዘንድ ከእርሱ ጋር የተተከልን ከሆነ በሞቱ ምሳሌ እንዲሁም ደግሞ እንሆናለን በትንሣኤው (ሮሜ ፮ ፣ ፫—፭) ።

መቃብር በመላ ሰውነትን የሚውጥ የሚያለብስም እንደመሆኑ ጥምቀት? ሲጠመቁ በመላ አካልን የሚውጥ አካልንም በመላ የሚያለብስ ውኃ መሆን አለበት ። በባሕረ ኃጢአት ሰጥሞ የነበረው አካል በተባረከው ውኃ ፫ ጊዜ ሰጥሞ ገብቶ ታጥቦ ሲወጣ ይነጻልና ።



እንዲሁም ጥምቀት ፪ኛ ልደት ስለሆነ ገንዳው ማኅፀነ ዮርዳኖስ መሆን ስላለበት ጥምቀቱ ጥልቅነት በአለው ገንዳ መሆን አለበት፤በተባረከው ውኃ በሥላሴ ስም ብቅ ጥልቅ እያሉ መጠመቅ ከሥላሴ ልጅነትን ያስገኛል፤ ከኃጢአትም ያነጻል፤ ልጅነትን ያድሳል። ጌታ ሲያስተምር ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለድን ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደማንገባ ገልጾ ይናገራል ፤ እርሱንም እንዲህ ሲል እናገኘዋለን ፤ «ኢየሱስ መለሰ እውነት እውነት እልሃለሁ ማንም ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባ ዘንድ አይችልም» (ዮሐ ፫ ፣ ፫—፭) ።

ለ/ የጥምቀት አመሠራረት ፣ ጥምቀት ለሰው ልጅ ሁሉ አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሣ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ መሥርቶታል ፤ እርሱም አስቀድሞ ራሱ በእደ ዮሐንስ በማየ ዮርዳኖስ ተጠምቋል (ማቴ፡፫ ፣ ፮—፯ ፣ ማር ፡፩—፲፩ ፣ ሉቃ ፡ ፫ ፣ ፳፩—፳፪ ፣ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፴፪—፴፫)። በኋላ ደግሞ ሁሉ ይጠመቅ ዘንድ ሲያጠይቅ ደቀመዛሙርቱን «ሒዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ ስታጠምቋቸውም በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም» ሲል አዟቸው እናገኛለን (ማቴ ፳፰ ፡ ፲፱) ።

እውነተኛውን ጥምቀት ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና የሚያሰጠውን እንዲህ አድርጎ ጌታ መሠረተው ። ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለዳችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ልትገቡ አትችሉም የሚለው አምላካዊ ቃል የሰው ልጅ የሆነው ሁሉ በግድ መጠመቅ እንዳለበት የሚያመለክት ነው።

ክርስቲያን ለመሆን ክርስቲያንም ለመባል ምሥጢራትንም ሁሉ ለመሳተፍ በጠቅላላውም ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመግባት የመጀመሪያው በር ጥምቀት ነው ፤ ስለዚህ ሰው ሁሉ በዚህ በር ማለፍ ግድ አለበት ። ያለጥምቀት ፍጹም ድኅነት እንደሌለ ጌታ ዐውቆ ጥምቀትን መሥርቶታል ። የተጠመቀ ብቻ እንደሚድን ፣ የተጠመቀም ብቻ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚሆን ጌታ ሲናገር «ያመነ የተጠመቀ ይድናል ፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል» ብሏል (ማር ፲፮ ፡ ፲፮) ።

ሐ/ ለጥምቀት የሚያስፈልጉ አንቀጾች፡— ምሥጢረ ጥምቀትን በትክክል ለመፈጸም ብዙ ነገሮች ያስፈልጋሉ ፤ ይሁን እንጂ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ያለነርሱም ጥምቀት ሊፈጸም የማይችል ፫ ነገሮች አሉ እነርሱም ፣

፩/ እምነት፡— ተጠማቂው ሰው አስቀድሞ የእግዚአብሔርን ሀልዎት መግቦት ማወቅ ማመንም አለበት ። እንዲሁም በባሕርይ በህል



www.ethiopianorthodox.org

ውና አንድ አምላክ ብሎ የሚያምነውን በአካል፤በስም፤በግብር ፫ ብሎ በሥላሴ ማመን በግድ ያስፈልገዋል። እንዲያውም የሥላሴ እምነት የተለየ የክርስቲያኖች እምነት ነው ፤ ስለዚህ ከጥምቀት ጀምረን የሥላሴን ስም እንጠራለን ፤ በሥላሴ እናምናለን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንጠመቃለን ።

እንዲሁም የወልድን አዳኝነት ፣ የአብ ቃል መሆኑንም ፤ ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ መወለዱን፤ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን ማመን ያስፈልጋል ። እንዲሁም «ልጄ የምወደው ይኸ ነው እርሱን ስሙት» ብሎ እግዚአብሔር አብ በተናገረው መሠረት ያስተማረውን ፣ የሠራውን ሁሉ ማመን ፣ መቀበል ፣ እርሱንም መከተል በግድ ያስፈልጋል ። ይኸን ሁሉ ለማወቅ ለማመን ትምህርት ስለሚያስፈልግ አዲስ ተጠማቂው አስቀድሞ ይህን ሁሉ ለማወቅ መማር አለበት ፣ እንዲሁም ይኸን ሁሉ ዐውቆ አምኖ መጠመቅ አለበት ።

ሳያምን መጠመቅ ግን እንደ መነከር እንጂ ከሥላሴ ለመወለድ አያበቃም ። በዕድሜ ከፍ ያሉ ይህን ሁሉ አጠናቀው ማወቅ ቀጥሎም ማመን ከዚያም በኋላ መጠመቅ ያስፈልጋል ። በዕድሜ ሕፃናት የሆኑት በወላጆቻቸውና በክርስትና አባቶቻቸው እናቶቻቸውም አማካይነት የምናጠምቃቸው እነርሱ ዋስ ወይም ተያዥ እየሆኑ ነው ።

እኛው እናስተምራቸዋለን ፣ እኛው ወደ ክርስቲያናዊ ሕይወት እንመራቸዋለን በማለት ተያዥ ሁነው ስለሚገቡ ነው ። ፪ኛ ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ ወደ ት/ቤት ፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን እናመጣቸዋለን ፤ ለካህን ፣ ለሰንበት ት/ቤት እንሰጣለን ሲሉ ነው ። ይኸ ካልሆነ ግን አጥማቂውም አስጠማቂውም ተጠማቂውም ይፈረድባቸዋል (ማቴ ፳፫ ፣ ፲፭)።

፪ኛ <u>በሥላሴ ስም መጠመቅ</u> ፣ ጥምቀት አስፈላጊ ነው ስንል እንዲሁ ዝም ብሎ ማጥመቅም መጠመቅም አይደለም ፤ በሥላሴ ስም ማጥመቅ እንጂ። ራሱ ጌታ በኔ ስም አጥምቁ ሳይል በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ብሎ በሥላሴ ስም ማጥመቅን ከፍተኛ አንቀጽ አድርጎ ነግሮናል (ማቴ ፳፰ ፣ ፲፱) ።

በዚህም መሠረት አጥማቂው ካህን ጸሎቱን በሚገባ ከፈጸመ በኋላ «አጠምቀከ በስመ አብ ፣ አጠምቀከ በስመ ወልድ ፣ አጠምቀከ በስመ መንፈስ ቅዱስ» እያለ የሥላሴን ስም እየጠራ ፫ ጊዜ ከውሀው ብቅ ጥልቅ ያደርገዋል ፤ ይኸም አንቀጽ ሊቀር ሊለወጥም የማይችል የማይገባውም ነው ።



፫/ <u>ጥምቀት በውኃ መሆን፡—</u> ማንኛውም ተጠማቂ ሁሉ ሀብት አለኝ ብሎ በማር በወተት በሌላም ቅባት ነክ ነገሮች ሊጠመቅአይችልም፤ ደግሞም አይገባውም፤ በውኃ ብቻ መጠመቅ ግድ ነውና ። ጌታ ራሱ በውኃ ተጠምቋል ፣ እንዲሁም በውኃ ብቻ ማጥመቅ እንደሚገባን ከውኃና ከመንፈስ ያልተወለደ መንግሥተ ሰማያትን ሊወርስ አይችልም ሲል ተናግሯል (ዮሐ ፣ ፫ ፣ ፫) ።

ሐዋርያትም ሁሉ በውኃ አጥምቀዋል ፤ የኢትዮጵያ ጃንደረባም በውኃ ተጠምቋል (የሐ ፣ ሥራ ፣ ፰ ፣ ፴፰) ።

፬/ <u>በካህን ብቻ መጠመቅ</u> ፣ ማንም ሰው በራሱ ሊጠመቅ አይችልም ፣ ያልሆነ ሰውም ሊያጠምቅ አይችልም በደንበኛው ካህን እንጂ ፤

፭/ <u>ለጥምቀት የተወሰነ ዕድሜ፡—</u> ማንኛውም ሰው ያለ ዕድሜ ገደብ መጠመቅ ያስፈልጋል ፤ ምክንያቱም ጌታ የተናገረው አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ አጥምቁ የሚል ነው እንጂ የዕድሜ ፣ የጾታ ፣ የኰሳ ገደብ ከቶ አላደረገም ።

የቤተ ክርስቲያን ሕግ ፍትሐ ነገሥቱም «ጥምቀትም የተሠራ ነው ለወንዶችም ለሴቶችም ፣ ለትንንሾችም ለትልልቆችም» ሲል ማንኛውም ሰው ሁሉ ሕፃናትም ሽማግሌም መጠመቅ ግድ እንዳለባቸው ያመለክታል (ፍት ፣ ነገ አንቀጽ ፫) ።

ሐዋርያትም በየደረሱበት ሁሉን ያጠምቁ ነበር እንጅ በዕድሜ በጾታ በሌላም መልክ እንደ ነበር የሚገልጥልን የለም ፣ ለምሳሌ ቅ/ጴጥሮስ ቆርኔሌዎስንና ቤተሰቡን እንዳጠመቀ እናገኛለን (የሐ ፣ ሥራ ፣ ፲ ፣ ፳፫) ። ቤተሰብ ሲል ዕለት ከተወለደ ሕፃን ጀምሮ እስከ ፹ ከዚያም በላይ ዕድሜ ያላቸው ሰዎች ሊገኙ ይችላሉ ፤ እንግዲህ ጴጥሮስ ሁሉንም አጠመቀ እንጂ በምክንያት የተወው የለም ።

ያልተጠመቀ አይድንም የሚለው አምላካዊ ቃል ሁሉም በጥምቀት ጥላ ሥር ማደር እንዳለበት ያመለክታል ። እንግዲያውስ ሕፃኑን ፣ ሽማግሌውን ፣ ወንዱን ሴቱን ሁሉንም ማጥመቅ እንጂ በዕድሜ ገደብ በሌላም ምክንያት ለይቶ መተው ተገቢ አይደለም ። ወንድ በ፵ ቀን ሴት በ፹ ቀን መጠመቅ እንዳለባቸው ቤተ ክርስቲያን ትናገራለች ፤ ወዲያው ግን የታመመና ሞት የሚያሰጋው ከሆነ ይኸ ሳይጠበቅ ማጥመቅ ተገቢ እንደሆነ ትናገራለች ። ይኸን ስንመለከት ደግሞ እንደተመቸ በማንኛውም ዕለት ማጥመቅ እንዳለብን እንጅ ገደቡን እያመለክትም ።



www.ethiopianorthodox.org

ሠ/ የጥምቀት ዋጋ ፡— ጥምቀት በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋን ያሰጠናል፤ማለት ውኃ በገንዳ ሆኖ ካህኑ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ ሲጸልይ በኋላም ሲያጠምቅ ይታያል ፤ይኸም የሚታይ አገልግሎት ይባላል ።

በጥምቀት አማካይነት ልጅነት ሲሰጥ ፣ ኃጢአቱ በቁራኝነት የመጣው ሲወገድ ፣ መንፈስ ቅዱስ ሲሰጥ አይታይም ፣ ይኸም የማይታይ ጸጋ ይባላል ።

ዋናው የጥምቀት ዋጋው የሥላሴ ልጅ ፤ የመንግሥተ ሰማያት ባለቤት መሆን ፣ በጥምቀት ታጥቦ ከኃጢአት ንጹሕ መሆን ነው ።

## ምዕራፍ ፱ ምሥጢረ ሜሮን ፣

ሀ/ የቃሉ ትርጉም ፡— ሜሮን ማለት ቅባት ማለት ነው ፤ ይኸም ሜሮኖ እቀባለሁ ከሚለው ግሪክኛ ቃል የወጣ ነው ። ይኸም ቅባት እንደማንኛውም ቅባትነት እንዳላቸው ቅባት አይደለም፤የተባረከ የከበረ ፣ ከጥንት ከሐዋርያት ሲያያዝ የወረደ ቅባት ነው እንጂ ፣

ለ/ አመሠራረቱ፡— ይኸ ምሥጢር በቅ/ሐዋርያት ጊዜ የተመሠረተ ነው ፤ ይኸውም አጥምቀው ሲፈጽሙ እጃቸውን ጭነው ሲጸልዩላቸው መንፈስ ቅዱስ ይወርድላቸው ነበር ፤ ግን በዚያን ጊዜ ቅብዓቱ እንደ ነበር የሚያጠይቀው ሐዋርያው ዮሐንስ «እላንት መቀባት አላችሁ ከቅዱሱ ፣ ሁሉንም አውቃችኋል» ሲል ተናግሯል (ዮሐ ፣ ፪ ፣ ፳)። እንደገናም በዚሁ ምዕራፍ ላይ «ከእርሱ የወሰዳችሁት መቀባት በእናንተ ትጸናባችኋለች ፤ ማንም ያስተምራችሁ ዘንድ አትሹም እንደዚሁ መቀባት ያስተምራችኋል እንጂ ስለ ሁሉ ፣ እርሱም እውነተኛ ነው» (ዮሐ ፣ ፪ ፣ ፳፯)።

ቅዱስ ጳውሎስም እንዲሁ «እግዚአብሔር የሚያጽናናን ከእናንተ ጋር በክርስቶስ ሃይማኖት የቀባንም እርሱ ነው ፤ እርሱም ደግሞ አተመነ የመንፈሱንም መያዣ በልባችን ሰጠን ሲል ተናግሯል ( ፪፡ቆሮ ፣ ፳፩—፳፪ ) ።

እኛም ሜሮንን ለአዲስ ተጠማቂዎች ስንቀባ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፣ብለን የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ እንደተቀበሉ ለማረጋገጥ ማኅተም አድርገን ነው ። ይኸንንም እንደገና ቅ/ጳውሎስ መስክሮ እንዲህ ሲል ጽፎ እናገኘዋለን «የእግዚአብሔርንም አዲስ መንፈስ ለመድኃኒት ቀን የታተማችሁበትን አታሳዝኑ» (ኤፌ ፣ ፬ ፣ ፴) ።



እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆናችን ምልክት ማኅተመ መንፈስ ቅዱስን እንታተማለን ፣ ቅብዐ መንፈስ ቅዱስን እንቀበላለን ፤ በዚህ በሚታየው አገልግሎት የማይታየውን ጸጋ እናገኛለን ።

ሐ/ የሜሮን ጥቅም፡— ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ለማግኘት ፣ ከእግዚአብሔር ለመወለድ ማረጋገጫው ማኅተመ መንፈስ ቅዱስን እናገኛለን ።

## ምዕራፍ ፲ ምሥጢረ ቊርባን

፩/ ብሂል

ምሥጢረ ቊርባን ማለት ጌታችን ኢየሱስ የመሠረተው፣ ያስተማረውና በመጨረሻም ማዕድ አቅርቦ እንኩ ብሉ ይኸ ሥጋዬ ነው ፤ እንኩ ጠጡ ይኸ ደሜ ነው ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ፤ በሥራም የገለጠው ፣ እስከዛሬም ያለ አድልዎ ለሁሉ የሚሰጠው የክርስቶስን ሥጋና ደም የመቀበል ምሥጢር ነው ።

ካህኑ ኅብስቱን በጻሕል ወይኑን በጽዋዕ አድርጎ የሚያቀርበው ፣ በጸሎትና በእግዚአብሔር ቃል ተለውጦ ኅብስቱ ሥጋ መለኮት ፣ ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት የሚሆነው ፣ ሕዝብ ለድኅነትና ለዘለዓለም ሕይወት የሚቀበለው ምሥጢረ ቊርባን ይባላል ።

ምሥጢረ ቊርባን ስንበላውና ስንጠጣው በኅብስትና በወይን መልክ ነው ፣ ግን በካህኑ ጸሎትና ቡራኬ ተለውጦ የክርስቶስ አካል ይሆናል ፤ ማለት ደሙ ፍጹም የክርስቶስ ደም በዕለተ ዓርብ የፈሰሰውን ፣ ሥጋውም በዕለተ ዓርብ የተቆረሰውን ይሆናል ፤ የዚህም ለውጥ እንዴት እንደሆነ ስለማይታወቅ ምሥጢር ተብሏል ።

እንግዲህ ክርስቶስ ሊቀ ካህናት ሁኖ ለአባቱ ያቀረበው ፤ ያሳረገው መሥዋዕት ስለሆነ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሁሉ ከዚህ ሥጋ መብላት ፣ ከዚህም ደም መጠጣት ግዴታ ነው ፣ ያለዚያ ተዋሕዶት የሚኖር ሕይወት የለውም ፤ ክርስቶስ ሲያስተምር አስቀድሞ «እኔ ነኝ የሕይወት እንጀራ ፣ ከሰማይ የወረደ ፣ ማንም ከዚህ እንጀራ የሚበላ ፣ ለዘለዓለም ይኖራል እኔም የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው » ሲል አስተምሮ ነበር(ዮሐ፡ ፮ ፣ ፶፬—፶፮) ። ከዚህም በማያያዝ «እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ እላንተ ሕይወት የላችሁም ፤ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ ለርእሱ የዘልዓለም ሕይወት



www.ethiopianorthodox.org

አለው ፣ እኔም በኋለኛው ቀን አስነሣዋለሁ ሲል ገልጦ ተናግሯል (ዮሐ. ፮ ፡ ፶፬) ። በዚህ መልክ ክርስቶስ ሲያስተምረው የቆየውን በመጨረሻ ጊዜ በተግባር ገለጠው ። ማለት የመጨረሻ እራት አድርጎ ሥጋውንና ደሙን «ንሡ ብሉ ይኽ ሥጋዬ ነው ፤ ጽዋውንም አንሥቶ አመስግኖ እንዲህ ሲል ለደቀመዛሙርቱ ሰጣቸው ፤ ከዚህ ጠጡ ይኽ ደሜ ነው ፤ ለአዲስ ኪዳን ለብዙ ሰዎች የሚሰጥ ኃጢአትን ለማስተስረያ» ሲል (ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፳፮—፳፰) ።

## ፪/ መቀረብ የሚገባው ማነው ?

በክርስቶስ ያመነ ክርስቶስንም የተከተለ ሁሉ የዕድሜ ፤ የጾታ ገደብ ሳይኖርበት በክርስቶስ ቃል መሠረት ሁሉም ከሥጋው መብላት ከደሙ መጠጣት ይገባዋል ። ምእመኑ ሁሉ ከክርስቶስ ጋር አንድነት ይኖረው ዘንድ ፣ እንዲሁም ሁሉም አንዱ ከሌላው ጋር አንድነት ይኖረው ዘንድ መቀረብ አለበት ። ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ከክርስቶስ ጋር የሚዋሐደው ሥጋውን በመብላት ደሙንም በመጠጣት ስለሆነ በግድ መቀረብ አለበት ።

## ፫/ ሁል ጊዜ መቀረብ እንደሚገባ

ምሥጢረ ቍርባን ከሚደጋገሙ ምሥጢራት ውስጥ ነው ፤ ስለዚህ ማንም ክርስቲያን በየዕለቱ ፣ በየሳምንቱ ፣ በየወሩ ፣ መቀበል አለበት ፤ ቢያንስ እንኳን በዓመት ፫ ጊዜ መቀረብ አለበት ።

ካህኑ በሚያቈርብበት ጊዜ «ሥጋሁ ለአማኑኤል አምላክነ ዘበአማን ዘነሥአ እም እግዝእተ ኲልነ» እያለ ፍጹም የክርስቶስ ሥጋና ደም መሆኑን እየመሰከረ ነው ። የሚቀበለውም ምእመን «አሜን» ልክ ነው አምናለሁ ብሎ ይቀበላል (ፍትሐ ፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፲፫፡ ቍጥር ፭፻፳) ።

ማንኛውም ምእመን ሲቈርብ ከሥጋው መብላት ከደሙም መጠጣት ግድ አለበት እንጅ አንዱን ተቀብሎ ፪ኛውን መተው ተገቢአይደለም፤ ምክንያቱም ክርስቶስ ሲያስተምር ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው ብሎ ከ፪ቱም መቀበል እንደሚገባ አስተምሯልና (ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፶፮) ።

በቍርባን ጊዜ ለሥርዓቱ መልክ እንዲኖረው፣ ዝብርቅርቅም እንዳይል መጀመሪያ ጳጳሳት ፤ ቀጥሎም ካህናት ፤ ቀጥሎም ዲያቆናት ፣ ቀጥ



ሎም ሕዝባውያን እንዲቈርቡ ሕግ ነው ። እንዲሁም ከሴቶችም በፊት ወንዶች እንዲቀበሉ ሕግ ያዛል (ፍትሐ ፡ ነገ፡ አንቀጽ ፲፫ ቍጥር ፭፻፲፱። ይኽም የሥነ ሥርዓት አጠባበቅ እንጂ ልዩነትን የሚያመለክት አይደለም።

## ፬/ እንዴት መቀረብ እንደሚገባ

ቅዱስ ቍርባንን የሚቀበሉ ሁሉ መጾም አለባቸው ፤ ይኸም ማለት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የውሎ ቅዳሴ ስላለ ጾሞ መዋል ስላለበት ነው ፤ የጧት ቅዳሴም ከሆነ በዋዜማው በጊዜ መብላት እንዳለበት ያመለክታል (ፍት፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፲፫ ፡ ፭፻፲፪—፭፻፲፫) ። እንዲሁም አስቀድሞ ንስሐ ገብቶ ኃጢአቱን ተናዝዞ ንጹሕ ሁኖ መቀረብ አለበት ።

ለቍርባን የሚሆነውን ኅብስትና ወይን ሌላውንም መብዓ ያመጡትን ሁሉ ካህኑ ስማቸውን በየጊዜው በጸሎት ማንሣት ተገቢ ነው (ፍትሐ ነገ ፡ አንቀጽ ፲፫ ቍጥር ፭፻፯) ።

ለመሥዋዕት የሚሆነው ኅብስት በየዕለቱ መዘጋጀት አለበት ፤ በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት በአደረ መሥዋዕት አይቀደስምና ።

ዛሬም የተሠራው ኅብስት በምንም መልክ ማደር የለበትም (ፍትሐ ነገ - አንቀጽ ፲፫ ቍጥር ፭፻፳) ።

ለቤተ ክርስቲያን የሚሆነውን መብዓ ፣ በተለይም ለቅዳሴ አገልግሎት የሚውለውን ስጦታ ምእመናን ከሆኑና በእምነታቸው በሥነ ምግባራቸው ከታወቁት ሰዎች ብቻ መቀበል ተገቢ ነው ፤ ከሌሎች ወገኖች ከሆነ እግዚአብሔር አይቀበለውምና (ፍትሐ ነገ፡ አንቀጽ ፲፫ ፣ ቍጥር ፭፻፩—፭፻፫ ) ። ለምሥጢረ ቍርባን አገልግሎት የሚውለው ኅብስት ከንጹሕ ስንዴ ብቻ የተሠራና ንጹሕ ወይን መሆን አለበት ፤ ለመሥዋዕት አገልግሎት ሌላ ቅብዓት የሆነ ወይም ሌላ ነገር ፣ ሥጋ ልዩ ልዩ ፍሬም ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲገባ አይፈቀድም ፤ ፈጽሞም ክልክል ነው (ፍትሐ ነገ ፡ አንቀጽ ፲፫ ቍጥር ፬፻፺፯ ቍጥር ፬፻፺፰) ።

## ምዕራፍ ፬/ ምሥጢረ ንስሐ ፡

### ፩/ ብሂል ፤

ንስሐ ማለት መጸጸት መመለስ ማለት ነው ፤ ይኸውም ነስሐ ካለው ከግእዝ የወጣ ቃል ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

አንድ ሰው ወዶና ፈቅዶ በሠራው ፣ ሳያውቅም በስሕተት ቢሆን ፣ ወይም ከልማድ የተነሣ የኃጢአት ዘርፍ ከሆኑት ነገሮች ሲሠራ ከቆየ በኋላ በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን ታርሞ ከቀድሞ ስሕተቱ ቢመለስ የቀድሞ ሥራውን ሁሉ ስሕተት መሆኑን ዐውቆ እንደገና አልመለስበ ትም ፣ አላደርገውም ፤ አላበጀሁም ብሎ ሲመለስ ንስሐ ይባላል ።

## ፪/ የምሥጢረ ንስሐ አመሠራረት ፣

ይኸንም ምሥጢረ ንስሐ ጌታ የመሠረተው ፣ ያስተማረውም ነው፤ በዚህም ምሥጢር የሰው ልጅ በሠራው ኃጢአት ያስወሰደውን ልጅነት ያስመልሳል ፣ የረከሰውን ሰውነቱን ያነጻል ያረጀውን መንፈሱን ያድሳል።

ንስሐ የበደለውን እንዳልበደለ ፣ ኃጢአተኛውን እንደ ጻድቅ ፣ ዘማዊውን እንደ ድንግል ያደርጋል ። ከሰው ልጅ የሚፈለገውም መመለሱ ፣ መታረሙ ነው እንጂ የእግዚአብሔር ምሕረት ዘላለማዊ ስለሆነ ማንኛውም በዳይ ቢመለስ ፣ ቢጸጸትም ፈጥኖ ይቅርታን ያገኛል ።

## ፫/ ማን ንስሐ መግባት እንደሚገባው ፣

ምሥጢረ ንስሐ ለካህንም ፣ ለሕዝባዊም ሁሉ አስፈላጊ ነው ፤ ምክንያቱም ሁሉም ሰው እንደመሆኑ የማይበድል የለምና ። እንዲሁም ሕፃናት አስበው ለመናገር ከቻሉበት ጊዜ ጀምሮ ክፉና ደግ መሥራት ይችላሉ ተብሎ ስለሚገመት በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ከ፲፪ ዓመት ዕድሜያቸው ጀምሮ ንስሐ መግባት ፍትሐት መፈታት ያስፈልጋቸዋል ። ከዚያ በታች ያለው ሕይወታቸው ግን ከመሠረቱ እንደ ንጹሕ ሠሌዳ ስለሆነ ንጹሐን ናቸው፤ ቢያጠፉም ዐውቀው ይሁንብን ብለው የሚሠሩት ስላልሆነ እንደበደል አይያዝባቸውም ።

ንስሐ ለሰው ልጅ ሁሉ አስፈላጊ መሆኑን ከተናገርን በኋላ የኑዛዜን አስፈላጊነት እንናገራለን ።

## ፬/ ኑዛዜ ፣

እንግዲህ ማንም ንስሐ ከገባ መናዘዝ በግድ አለበት ። መናዘዝም ማለት ዐውቆና ወዶ ሳያፍር የሠራውን በደል ሁሉ ሳያፍር መናገር መለፍለፍ ፣ የጥፋቱን ዝርዝር ሁኔታ መነሻ ምክንያት ከተግባሩ ጋር ለካህኑ መናገር ማለት ነው ።

ኑዛዜ ራስን መክሰስ ፣ መውቀስ ማለት ነው ፣ አንድ ክርስቲያን ክርስቶስ ከካሰለት በደሙም ከዋጀው በኋላ የርሱን ውለታ ዘንግቶ ንጹሑን



አካሉን በኃጢአት ማቆሸሽ ስለሆነ ራሱንም ክርስቶስንም መበደሉን ማ
ወቅ አለበት ፤ ስለዚህ ራሱ ተከሳሽ ሆኖ ካህኑን ታዛቢ ዳኛ አድርጎ በእ
ግዚአብሔር ፊት መቆም ማለት ነው ።

በእርግጥም ተነሳሒውና እናዛዡ ካህን በግልጥ ሲታይ የይቅርታ
አምላክ እግዚአብሔርም ፫ኛ ሁኖ እንደሚገኝ ይቅርም እንደሚለው አምኖ
መናዘዝ ነው ፤ በዚህም መሠረት ኑዛዜ በካህን ፊት መፈጸም አለበት ።
ጌታ ራሱ ሲናገር «እናንተ ኃጢአቱን የያዛችሁበትን እኔም እይዝበታ
ለሁ ፤ እናንተ ይቅር ያላችሁትን ደግሞ እኔም ይቅር እለዋለሁ» እያለ በሐ
ዋርያት አማካኝነት ለካህናት አስተላልፏል ።

ለምሥጢረ ንስሐ የሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ አለው ፣
ይኸም ተነሳሒውራሱን በእግዚአብሔር ፊት አዋርዶ ሲያለቅስ፣ሲጸጸት፣
በደሉን ሲናገር ፣ ሲያውቅ በድፍረት ፣ ሳያውቅ በስሕተት መሥራቱን
በካህኑ ፊት ሲናዘዝ ይታያል፤ ካህኑም የተነሳሒውን ኑዛዜ በጽሙና ከሰማ
በኋላ ከእግዚአብሔር ይቅርታን ሲጠይቅለት ፣ ሲጸልይለት ይታያል ፤
ይኸ የሚታይ አገልግሎት ይባላል ።

ይኸም የሚታይ አገልግሎት ከነምሳሌው ፣ ከነምልክቱ መጠበቅ፣
መፈጸምም ያለበት ነው ፤ ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት እው
ነተኛውም ትምህርት ነውና ።

ሰውየውም ከልብ መመለስ ፣ መጸጸትና መናዘዝ የተነሣ ፣ ከካህኑም
ጸሎትና ምልጃ የተነሣ እግዚአብሔር እንደ ቃል ኪዳኑ በደሉን ይቅር
ይለዋል ፤ ኃጢአቱን ያስተሠርይለታል ። ይኸ ሁሉ ሲሆን፤ ጸጋውና በረ
ከቱም ሲሰጠው አይታይም ፤ ስለዚህ ይኸ የማይታይ ጸጋ ይባላል ፤ ይኸ
ደግሞ መታመን ያለበት ነገር ነው ፤ ማለት ማንም በደለኛ ራሱ ከተመለሰ
እግዚአብሔር ለመመለስ ከበደሉም ለማንጻት ዝግጁ መሆኑን ማመን አለ
ብን ።

## ፭/ የኃጢአት ዓይነቶች ፣

የኃጢአት ዓይነቱ ፣ ስልቱ ብዙ ሲሆን ተጠቃሎ በ፫ ይከፈላል ፤
ይኸውም የሐልዮ ለብቻው አንድ ሲባል የነቢብ ፣ የርእይ ፣ የተናግሮ
አንድ ወገን ሆኖ ፪ ይባላል ፤ ገቢርም ፫ኛ ይሆናል ። የኃጢአት መሠረቱ
ሐልዮ ነው፤ምክንያቱም ማንኛውም ኃጢአት ሳይታሰብ የሚሠራ የለምና።
አንዳንድ በድንገተኛ አጋጣሚ ሳይታሰብ የሚፈጸም ቢኖር ብዙ ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

አይጠየቅበትም ፤ በንዝህላልነቱ ባለመጠንቀቁ ግን ይቀጣል ፤ ስለዚህ የኃጢአት ሥር የሆነውን ሐሳቡን የሰው ልጅ ሁሉ ማራቅ አለበት ፣ ገና ሲታሰብ የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት ሰይጣንን በማውገዝ ወዲያው ራሱን ማረም አለበት ።

አንድ በደል የሆነን ነገር በየጊዜው ማሰብ ለመሥራት ፈቃደኛነቱን ይገልጣል ፤ ሱስም ይሆንበታል ፤ ይኸም እንደተፈጸመ ያስቈጥራል ፤ ማለት ለመፈጸም ያስቸገረው የጊዜ የቦታ ፣ የሁናቴ ጉዳይ ነውና ። እንዲያውም ብዙ ካወጣና ካወረደ በኋላ ለመሥራት ፈቅዶ ባለቤት ነቅቶበት ፣ ውሻ ጮሆበት ፣ አጥር ቅጥር በርትቶበት ፣ በጠቅላላም ከዐቅሙ በላይ የሆነ ነገር ገጥሞት ቢመለስ እንደፈጸመው ፣ ፍጹም በደልንም እንደሠራ ይቈጠራል ።

እንዲሁም መንገድ ሲሄድ ፣ ወይም ባለበትም ቦታ ሆኖ ክፉ ነገርን ያያል ፤ ይሰማል ፤ ወይም ይናገራል ፤ ይኸ በደል እንደሆነ ተገንዝቦ የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ ሰይጣንን አውግዞ የተወው፤ያልመላለሰው እንደሆነ እንደበደል አይቈጠርበትም ፣ ግን አሁንም ስለዚያ ነገር ለመመልከት ፣ ለመስማት ፣ ለመናገር የጓጓ እንደሆነ ያም ነገር እንዲፈጸም የተነሣሣ እንደሆነ አሁንም ይኸን ሁሉ በሥራ ላይ እንዳዋለው ፣ በደልንም እንደፈጸመ፤ኃጢአትንም እንደሠራ ይቈጠርበታል ። ገቢርም ሆኖ ሳይታሰብ የተፈጸመ ሁሉ እንደበደል የማይሆንበት ምክንያት አለ ፤ ይኸንም ከፍ ብለን ገልጠነዋል ፤ ግን እንደሁናቴው የሚያገኘው ቀኖና ይኖራል ።

## ፮ ቀኖና

ካህኑ የተነሳሒውን ንስሐውን ተመልክቶ ፤ ኑዛዜውን ሰምቶ ፤ ከእግዚብሔር ምሕረት ለምኖ፤ይቅርታ አሰጥቶ ብቻ አይተውም ፤ ግን እንደ ኃጢአቱ ከባድነትና ቀላልነት ፣ እንደ ተነሳሒው ደካምነትና ብርታት ቀኖና ይሰጠዋል ። ምንም ኃጢአት ሁል ጊዜ ኃጢአት ቢሆን ከባድና ቀላል አለው ፤ እንዲሁም ከተነሳሕያን ውስጥ ለኃጢአት ብርቱ ለንስሐ ደካማ የሆኑ ይገኛሉ ። ይኸም በመጽሐፈ ቀኖና የተወሰነ ቢሆንም የካህኑን ፈሊጥና ዕውቀት ይጠይቃል ፤ ኃጢአቱ በንስሐውና በኑዛዜው በካህኑም ጸሎት እንደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተሰርዮለታል ፤ ቀኖናው ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ፤



፭/ ተነሳሒው ስሕተትን በሚያመጣው ወጥመድ ደግሞ እንዳይያዝ ለማስጠንቀቂያ ለሌሎችም መለበሚያ እንዲሆን ቤተ ክርስቲያን የወሰነችው ቅጣት ነው ።

፮/ አዝኖ ደስታ ፣ ጹሞ ፋሲካ ሲሆን ለራሱም ይቀለዋል ፤ ይደሰትበታልና ፣ ምሥጢሩን ማቃለል እንዳይሆን ይኸ ዓይነት ቀኖና ይሰጠዋል ።

ቀኖናውም ቅዱስ መጽሐፍን በተወሰኑት ዕለታት በማንበብ እንዲያሳልፍ ፣ ከሰው ጋር ሳይገናኝ በጸሎት ጽሙድ ሆኖ እንዲቆይ ፣ የተወሰኑ ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም እንዲወጣና እንዲወርድ በማድረግ፤ጾም ጸሎት በመያዝ የተወሰኑ ዕለታት ሳምንታት ፣ አውራኀ በመስጠት ፣ ምጽዋት እንዲሰጥ ፣ በጉልበቱ በዕውቀቱ ሌሎች ችግረኞችን እንዲረዳ በማድረግ ፣ ይኸን በመሳሰሉ በሌሎች ተግባሮች ይፈጸማል ።

ኑዛዜው በሥውር ካህኑና ተነሳሒው ከእግዚአብሔር ጋር የሚያደርጉት ውይይት ሲሆን ፤ አንዳንድ ጊዜም በዐደባባይ የሚሆን አለ ፤ ሰውያወቀው ፀሐይ የሞቀው ግልጥ የሆነ አድራጎት እንደሆነ ቀኖናውም ግልጥ መሆን አለበት ፤ ምክንያቱም ፣

ሀ/ ሌላው እንደታዛቢ ሆኖ እንዳይገምት ማለት እንዲሁ የወጣ እንዲሁም የገባ መስሎ እንዳይታይ ፣

ለ/ የሰው ፊት እሳት ስለሆነ ከባድን ኃጢአት በሕዝብ ፊት ሲናዘዝ መልሶ እንዳይደግመው ቁርጠኛ መሆኑን ሲናገር በበለጠ ራሱን የሚክስ፤ራሱን የሚያጋልጥ ሆኖ በመገኘቱ ፍጹም ይቅርታን እንዲያገኝ ።

ሐ/ ሌላው ሕዝብ እንዲቀጣ፤ማለት አሳፋሪ አስፈሪም ነገር መሆኑን ዐውቆ ሁሉም እንዲጠነቀቅ ፣ ይኸንንም የመሰለውን አድራጎት ወደ መፈጸም እንዳያዘነብል መቀጣጫ ለማድረግ ነው ።

## ፯/ የንስሐ መስጫ ቦታ

ኑዛዜ መፈጸም ያለበት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምሥጢር ቦታ፣ በእውነት በቅንነት ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ ነው። ለይቅርታ ምክንያት መሣሪያም ሆኖ የቀረበውም ካህን እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆነ ፣ ከልቡ ለተነሳሒው የሚጸልይ ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ ችሎታ ያለው ንጽሕናን ቅድስናን ገንዘብ ያደረገ መሆን አለበት ። ለእግዚአብሔር ምሕረት መተላለፊያ እውነተኛም መሣሪያ ሆኖ መገኘት አለበት።



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፰ ምሥጢረ ክህነት

### ፩/ ብሂል ፡

ምሥጢረ ክህነት የማሠርና የመፍታት ሥልጣን ያለው ከመሆኑም በላይ ሌላውንም የቤት ክርስቲያን ምሥጢራት ለመቀደስ፤ለማክበር፤ለመፈጸም ችሎታ ያለው እርሱ ብቻ ነው ። ክርስቶስ የሠራው የመሠረተውም ምሥጢር ከመሆኑም በላይ ከርሱም ጀምሮ እስከ ዛሬ ያለማቋረጥ ሲተላለፍ የሚገኝ ነው ፤ ይህንም ሥልጣን ክርስቶስ ለተከታዮቹ ለሐዋርያት ሰጥቷል ፣ ሐዋርያትም ለተከታዮቻቸው በአንብሮተ እድ እያስተላለፉእስከኛ ድረስ ደርሷል ፡ ከኛም እስከ ምጽአት እንዲሁ ያለማቋረጥ እንደሚሰጥ የተረጋገጠ ነው ። ይህንም ምሥጢር ክርስቶስ እንደ መሠረተው በቅዱሳት መጻሕፍት የተመሰከረ ነው (ማቴ ፲ ፡ ፮ ፡ ፲፰—፲፱ ፣ ዮሐ ፡ ፳ ፳፪—፳፫) ።

### ፪/ የምሥጢረ ክህነት ጥቅም

ምሥጢረ ክህነት ሀብትን ያሰጣል፤የማሠርን የመፍታትን ሥልጣን ያስገኛል ፤ እንዲህም ስንል ፤

፩ኛ/ አገልግሎቱ ፍጹም መሆን አለበት፣ውስጣዊ ሥራውም ከልብ እንዲሠራ ጸሎቱም ከልብ እንዲጸለይ ያስፈልጋል ።

፪ኛ/ ምሥጢሩን የሚፈጽመው ሰው ሁል ጊዜ ደንበኛ ካህን መሆንና በእውነት ቤተ ክርስቲያን የመረጠችው በሚገባም በአንብሮተ እድ የተሾመ ካህን መሆን አለበት ።

፫ኛ/ ምሥጢሩ የሚፈጸምለትም ሰው ከልቡ የተዘጋጀ ልቡን ከሕዝባዊነት ተራ ያወጣና የለወጠ፤ወደ መንፈሳዊ ዓለም ያዞረ፤የእግዚአብሔርን ጸጋ ከልቡ የፈለገ መሆን አለበት ። እነዚህ የተዘረዘሩት ነገሮች በሚገባ የተፈጸሙ እንደሆነ ከታሰበው ዓላማ በትክክል ይደረሳል ፤ የተፈለገውም ዋጋ ይገኛል ። ይኸ አገልግሎት በማንኛውም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ በጥብቅ ሊታሰብበትና በዚህም መልክ ሊደረግ የሚገባው ነው ፤ በተለየ ምሥጢረ ክህነት የበለጠ ጥንቃቄ የበለጠም አፈጻጸም ሊኖረው ይገባል ፤ ምክንያቱም ሌላውን ምሥጢር የሚቀድስ ወደሌላው ስቦ የሚያደርስ በምሥጢረ ክህነት የከበረ ካህን ነውና ።

### ፫/ ምሥጢረ ክህነት ክርስቶስ የመሠረተው ነው ፤

የክህነትን ጸጋ ክርስቶስ በመጀመሪያ ለቅዱሳን ሐዋርያት አደላቸው «ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውም መንፈስ ቅዱስን ተቀብሉ ኀጢአቱን



የተዋችሁለት ቀረችለት የያዛችሁበትም ሰው ተያዘችበት » (ዮሐ ፳ ፡ ፳፪ —፳፫ ፤ ማቴ ፲ ፡ ፩—፵፪፤ማር፤ ፮፡ ፯—፲፫፤ሉቃ ፱፡ ፩—፭)።«እርሱም ሰጠ እኩሊቶች ነቢያት ሌሎችም ሰባኪዎች ሌሎችም ጠባቂዎች - - -» (ኤፌ፡ ፬ ፡ ፲፩)።እያለ ቅዱስ ጳውሎስም ይመሰክራል።«አሁንም ለራሳቸው ተጠንቀቁ ለመንጋውም ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በርሱ ላይ ጠባቆች አድርጎ የሾማችሁ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ እርሱ በደሙ የዋጃትን» (የሐዋ ሥራ ፳ ፡ ፳፰) ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ያስረዳል ።

ክርስቶስ ይኸን የከበረ ሥልጣን ለሐዋርያት የሰጣቸው በነርሱ ብቻ እንዲወሰን አይደለም ፤ ለነርሱ ብቻ ቢሆን «እኔ እነሆ ከላንተ ጋራ ነኝ በዘመኑ ሁሉ እስከ ፍጻሜም ዘመን ሁሉ» (ማቴ ፳፰ ፡ ፳) ብሎ ባልመሰከረም ነበር ፤ ምክንያቱም ሐዋርያት ሁሉ በአንደኛው መቶ ዓመት ውስጥ የሞቱ ሲሆን ፣ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከናንተ ጋራ ነኝ ባላለም ነበር ። ነገር ግን ሐዋርያት ለተከታዮቻቸው እንዲያወርሱ፤በአንብሮተ እድ እንዲሾሙ ይህ ማዕርገ ክህነትና ሌላውም ሀብት ሳይቋረጥ እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚሰጥ መሆኑን የሚያረጋግጥ ቃል ነው።ስለዚህ ሐዋርያት ወዲያውኑ በአንብሮተ እድ ሰባቱን ዲያቆናት ሾሙ (የሐዋ ሥራ ፮ ፡ ፫ ፡ ፱)።ቀጥለውም ሁሉም በየሔዱበት ሀገረ ስብከት ዲያቆን ፣ቄስ ኢጲስ ቆጶስ ሾሙ(የሐዋ ሥራ ፲፬፡፳፫) ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለኤፌሶን ኤጴስ ቆጶስ አድርጎ እንደሾመው (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፬) እናገኛለን ። የኤጲስ ቆጶስነቱም ምልክት እርሱ እንዲሾም ሥልጣን ሰጥቶ ነበር ፤ «በተሰጣችሁ ጸጋ በትንቢት በቀሳውስትም ላይ እጅን በመጫን ቸል አትበሉ» (፩፡ጢሞ፡፬ ፡ ፲፬)። እንዲህ አድርጎ የሚመክረው ጢሞቴዎስን መጀመሪያ እርሱ በአንብሮተ እድ ከሾመው በኋላ ነው ፤ « ስለዚህ አሳስብሃለሁ የእግዚአብሔርን የጸጋውን ሕይወት ለማደስ ያደረችብህ ፣ በተሰጠኸው እጅን በላይህ በጫንኩብህ ጊዜ» (፪፡ ጢሞ ፩፡ ፮) ። እንዲሁም የቀርጤስ ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ቲቶን ሹሟል « ስለዚህ በቀርጢስ ተውኩህ የጎደለውን ሁሉ ትሞላ ዘንድ ቀሳውስትንም ትሾም ዘንድ ፣ በየሀገሩ እንዳዘዝኩህ» (ቲቶ ፩ ፡ ፭) ። ይህን የመሰለ ቅ/ሐዋርያት በየሔዱበት አገር ሰው እየመረጡ በአንብሮተ እድ እየሾሙ እስካሁን ይተላለፋል ፣ እስከ ምጽአትም ይህ ጸጋ ሳይጎደል ወይም ሳይቋረጥ ይሰጣል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፮ ምሥጢረ ተክሊል ፡

### ፩/ ብሂል

ጋብቻ በሕገ ቤተ ክርስቲያን አስተያየት እንደ ምሥጢር ሲታይ የቤተሰብእ ፡ የሕዝብ ፡ የመንግሥት መሠረት ስለሆነ ፡ ትልቅ ዋጋ አለው ፤ ስለዚህ ከዚህ ቀጥለን ሰፋ አድርገን ጋብቻ የሚፈጸምባቸውን አኳኋኖች እንመረምራለን ።

ይሁን እንጅ የጋብቻ ደንብ ለማኅበራዊ ኑሮ ያለውን ጥቅምና አስፈላጊነት ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ተረድተው በብዙ አስተያየት ሊደገፉት ይገባል ።

በቤተ ክርስቲያን ሕግ ውስጥ የጋብቻ ሕግ የሚለው ከቤተሰብ ሕግ ውስጥ ልዩ ክፍልን ይዞ ይገኛል ።

ተክሊል ማለት ወንድና ሴት ተስማምተው በሚያደርጉት ጋብቻ ካህን የሚሠራው የሚፈጽመውም፤ጸጋንና በረከትን የሚያሰጥ መንፈሳዊ አገልግሎት ነው ። ይህም ምሥጢር በሥጋዊ ጠባይ አስፈላጊነት ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን ፡ መንፈሳዊ ዓላማ ያለው ፤ ለዘር መብዛትን ፤ ለኑሮ ሕይወትን እንዲያስገኝ ቅዱስ እግዚአብሔር ፈቃዱ ኹኖ ያዘዘው የሠራውም ምሥጢር ነው ፤ ማለት በመጀመሪያው በጥንተ ፍጥረት ሴትና ወንድ በጋብቻ ሥርዓት አንድ ኹነው መኖር እንዲገባቸው አዳምና ሔዋን በመፍጠሩ ይታወቃል (ዘፍ፡ ፪-፳፩) ። እንዲሁም ከሥቱ አካላት አንዱ የአብ ቃል ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ የመጀመሪያ ታምራቱን የገለጠበት አንድ ወንድ በአንዲት ሴት ኹነው በሚጋቡት በቅዱስ ጋብቻ ነው (ዮሐ ፪፡ ፩—፲) ። እንዲሁም ክርስቶስ ሲያስተምር ፈሪሳውያን ሊፈታተኑት ጋብቻን እያቃለሉ ሲጠይቁት ጋብቻ ቅዱስ ሥራ እግዚአብሔር የባረከው፤እግዚአሔር የፈቀደው እንደ ሆነና እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ማንም ለመለየት እንደማይችል በሰፊው አስረድቷል ። ሰው ማግባት እንደሚገባው ፡ ጋብቻም ክቡር እንደሆነ ሐዋርያት ለጠየቁት ጥያቄ « - - - - ይህ ነገር ለሰዎች ኹሉ አይቻላቸውም ለተሰጣቸው በቀር ጃንደረባ ሁነው ከናቶቻቸው የተወለዱ ሰዎች አሉና ፡ ሌሎችም ሰዎች ሰልበው ጃንደረባ ያደረጓቸው አሉና ፡ ስለ መንግሥተ ሰማያት ሰውነታቸውን ጃንደረባ ያደረጉ ሰዎች አሉ ፡ ማስተዋል የሚችል ግን ያስተውል» (ማቴ ፲፱ ፡ ፲፪) ሲል የሰጠው መልስ ያስረዳል ፡ ማለት በንጽሕና ፡ በድንግልና ሊኖሩ እግዚአብሔር ከፈቀደላቸው ሰዎች በቀር ሰዎች ኹሉ በጋብቻ እንዲኖሩ ይህ ቃል ያስረዳል ።



### ፪/ የምሥጢረ ተክሊል የሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ

ምሥጢረ ተክሊልም እንደሌሎች ምሥጢራት የሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ አለው፤ ሙሽራውና ሙሽራይቱ ነጭ ልብስ ለብሰው፤ አክሊል ተቀዳጅተው፤ወደውም ለመጋባታቸው ቃል ኪዳን ሲገቡ፤ካህኑም ስለ አንድነታቸው ሲጸልይባቸው ፡ ሲባርካቸውም ቅዱስ ዘይትንም ሲቀባቸው ይታያል ። እንዲሁም የተፈጥሮ ጋብቻ ሲቀደስ፤ኹለት የነበሩ በመንፈስ ቅዱስ አንድ ሲሆኑ ፤ በኹለቱም ላይ ፍጹም ፍቅር ሲያድርባቸው ፤ መለያየት ሲጠፋላቸው አይታይምና ።

ማንኛውንም ምሥጢር ካህናት እንደሚፈጽሙት ይህም ምሥጢር እንዲሁ በካህናት ሊፈጸም ይገባዋል ። ካህኑ በበለጠ ሊያስብበት ሊጠነቀቅበት የሚገባ በምሥጢረ ተክሊል ነው ፤ ምክንያቱም ለሌላው ምሥጢር ኹሉ ሕዝብ ተሳታፊ የሚሆን ጋብቻ የከበረ እንደሆነ ነው ፤ ጋብቻ ሲረክስ፤ዘር ሲቀነስ ቤተ ክርስቲያንም አብራ ትረክሳለች ፤ አባሎቿም፣ይቀነሳሉ ፤ ለመንግሥት ጸጥታው ሊረጋገጥ ሰላም ጤንነት ሊገኝ አይችልም ። ሰው ሕግን የተላለፈውን ያህል ችግር መከራ ፈተና ያገኘዋል፤ስለዚህ አስቀድሞ ሁሉ በሕግ እንዲያገባ ፡ በጋብቻውም ጊዜ ልዩ ጸሎት እንዲደረግለት መለያየታቸው እንዲጠፋ መድከም የካህኑ ዋና ተግባር ነው ።

### ፫/ ጋብቻ የማይፋታ ምሥጢር መሆኑ

የመጀመሪያው ሰው አዳም ሔዋንን ብቻ አግብቶ በደስታ ጊዜ በገነት፤ በመከራ ጊዜ በምድረ ፋይድ አብረው ይኖሩ ነበር ። በምቾት ምክንያት ሚስት መፍታት የሚገባ ቢሆን አዳም በገነት ሳለ ሔዋንን በፈታትና ባበራት ነበር፣ወይም በመከራ ጊዜ መፍታት የሚገባ ቢሆን ምድረ ፋይድ በገቡ ጊዜ ባበረራት ነበር ። ወይም ብዙ ሴት ማግባት የሚገባ ቢሆን ሥላሴ ለአዳም ብዙ ሴት መፍጠር በቻሉ ነበር። ብዙ ወንድ ማግባት የሚገባም ቢሆን ኖሮ ለሔዋን ሥላሴ ብዙ ወንድ በፈጠሩላት ነበር ፤ ነገር ግን አንድ ወንድ በአንዲት ሴት ፡ አንዲት ሴትም በአንድ ወንድ መኖር በደስታም በመከራም አብረው መኖር እንደሚገባቸው ሲያጠይቅ ለሔዋን አዳምን ብቻ ፤ ለአዳምም ሔዋንን ብቻ ፈጠሩ (ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፳—፳፪) ። በኋላም ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሲያስተምር ይህኑ አጽንቶ «አላነበባችሁምን እግዚአብሔር አስቀድሞ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠረ ፤ ዓለም ፤ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ምሽቱንም ይከተላል ፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ፤ ሁለትም አይደሉም ፡ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየውም» (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፬—፮) ሲል በሰፊው አስረድቷል ።



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር በጥንተ ፍጥረት አንድ ያደረገውን ጋብቻ በበደል ምክንያት ብዙ ማግባት ብዙ መፍታት መጣ ፤ ይህም በሰው ላይ እግዚአብሔር ካመጣው ቅጣት አንደኛው ነበር ። በኋላ ግን አምላክ ሰው ኹኖ ሥጋን ለብሶ ፥ የተረገመውን ማኅፀን ቀድሶ፤ ያረጀውን አካል አድሶ፤ የአዳምን ልጅነት መልሶ ጋብቻ እንዲሁ የጸና እንዲሆን አውጇል ። ሐዋርያትም ይህን ተከትለው ጋብቻ ቅዱስ ምሥጢር ሲሆን መፋታት የማይቻል የማይገባም መሆኑን አጽንተው አስተምረዋል ። ባልና ሚስት ሊለያዩ የሚችሉበት ዋናው ምክንያት ሞት ብቻ ነው፤ይህንም የመሰለ የሥነ ምግባር ሞት ነው፤ ማለት ፩ኛው ወገን ዝሙት በሠራና እምነት ባጐደለ ጊዜ ነው ።

ዘርን ለማብዛትና ጸጋን ለመስጠት የሁለቱን አንድነት ለማጽናት እምነትን ፍቅርን ለማሳደር የተክሊል ጸሎት አስፈለገ ። መጀመሪያ እግዚአብሔር ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ ሲፈጥራቸው አንድ ሁነው ተረዳድተው ፥ ተደስተው እንዲኖሩ የሁሉም ገዥ ፥ የሁሉም አዛዥ ሁነው እንዲኖሩ ዘራቸው፤በዝቶ ምድርን መልተዋት እንዲኖሩ ነውና «እግዚአብሔር ሰውን ፈጠረ በመልኩ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ፤ እግዚአብሔርም ባረካቸው እግዚአብሔርም አላቸው ፤ ብዙ ተባዙም ምድርን ምሏት ግዟትም ፤ - - - » (ዘፍ ፩ ፥ ፳፯—፳፰ ) በቤተ ክርስቲያን በሚደረገው ጋብቻም የሚጸለየው ጸሎት ይህን የመሰለ ነው ።

## ፬/ የተክሊሉ ጥቅም ፤

ሁለትነት ጠፍቶ አንድነት እንዲመሠረት ፤ የባልና የሚስቱ ፍቅራቸው ፍጹም እንዲሆን ፥ የባልና የሚስትነታቸው እምነት እንዲከበር ነው ።

# ምዕራፍ ፯ - ምሥጢረ ቀንዲል

## ፩/ ብሂል ፤

ቀንዲል ወይም ቅብዐ ቅዱስ የተባለው ምሥጢር ከንጹሕ ወይራ ዘይት የተሠራ ፤ የሥጋንም የነፍስንም በሽታ የሚያርቅ ፤ የማዳን ኀይል ያለው፤ክርስቶስ የመሠረተው ፥ ሐዋርያትም ያስተማሩት ምሥጢር ነው ።

## ፪/ መቼ እንደተመሠረተ ፤

ክርስቶስ እንደ መሠረተው ምንም እንደ ሌሎች ምሥጢራት ግልጽ የሆነ ጽሑፍ እንኳን ባይገኝ ሐዋርያትን እንዳዘዛቸው ፥ እነርሱም ዘይትን እየቀቡ ብዙ ድውያንን እንዳዳኑ ከዚህ የሚከተለው ጽሑፍ ያስረዳል ፤



«በወጡም ጊዜ አስተማሩ ፤ ንስሓ ይገቡ ዘንድ እጅግም ሰይጣናትን አወጡ ፤ በዘይትም ብዙ ድውያንን ቀቡ ፤ አዳኗቸውም» (ማር፥ ፩ ፥ ፲፮)፤ ሐዋርያት ግን ይጠቀሙበት እንደ ነበር ከላይ የተዘረዘረው ብቻ ሳይሆን ቅዱስ ያዕቆብ፤«ማንም ከእናንተ ቢታመም የቤተ ክርስቲያን ቀሳውስትን ይጥራ ፤ ይጸልዩበትም ፥ በዘይትም ፥ ይቀቡት ፤ በጌታ ስም ፤ የሃይማኖትም ጸሎት ድውዩን ትፈውሰዋለች ፥ ጌታም ያስነሣዋል ፤ ኃጢአትም ሠርቶ እንደሆነ ትሰረይለታለች - - - - » ተገቢ መሆኑን (ያዕ፥ ፭ ፥ ፲፭—፲፮) ሲል ክርስቲያን ሁሉ ሊጠቀሙበት አስፈላጊና በሰፊው ያስረዳል ።

የማዳን ኃይል አለው ስንል ከዘይቱ የተገኘ ኀይል አይደለም፤ በእግዚአብሔር ጸጋ በቄሱ ጸሎት ነው ፤ ስለዚህም ያዕቆብ «የእምነት ጸሎት በሽተኛውን ያድናል ፤ ኃጢአቱንም ያስተሰርያል» ሲል በቅን ልቡና በንጹሕ ሰብእና ሆነው አምነው የጸለዩበት ዘይት ታምራት እንዲሠራ ፤ ኀይለ እግዚአብሔርም እንደሚገለጥ ያስረዳል ።

## ፫/ የምሥጢረ ቀንዲል አገልግሎት ፤

ምሥጢረ ቀንዲል እንደ ሌሎች ምሥጢራት በካህን ብቻ የሚፈጸም ምሥጢር ነው ። የተወሰነውን ጸሎት ካህኑ በሚገባ አድርሶ የበሽተኛውን አካል በመስቀል ምልክት ግንባሩን ፥ ሁለቱን ወገን ፊቱን ፥ ሸንጎበቱን ፤ የቀኝና የግራ እጁን በውጭም - በውስጥም ፪ እግሩን ፥ ቢቻል ታላላቅ ሕዋሳቱን ያለዚያም ለጊዜው የሚያመውን አካሉን ይቀባዋል ፤ በዚህ ጊዜ በሽታው ይለቀዋል ፤ ኀጢአቱም ይሰረይለታል ። ደዌ ሥጋ ለደዌ ነፍስ ፥ ደዌ ነፍስም ለደዌ ሥጋ ይተርፋሉና ማለት ንጽሕናቸውን ባለመጠበቃቸው ሰውነታቸውን በማጎሳቆላቸው ነፍሳቸውንም አብረው ያጎሳቁላሉ ፤ ሥጋቸው በታመመ ጊዜ ነፍሳቸውም አብራ ትታመማለች ፤ ግን ንስሐ ገብተው ፥ ተመልሰው ምሥጢረ ቀንዲልን የተቀበሉ እንደሆነ ድኅነተ ሥጋንም ድኅነተ ነፍስንም ያገኛሉ ።

## ፬/ የሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ ፤

በምሥጢረ ቀንዲልም የሚታይ አገልግሎት የማይታይም ጸጋ አለው፤ ማለት በሽተኛው ወድቆ ድኅነትን ደጅ ሲጠና ፤ በንጹሕ ዘይት ላይ የሃይማኖት ጸሎት ሲጸለይ ፥ ቄሱ ሲባርከው ፥ ከጸሎቱም በኋላ አካሉን ሲቀባው ይታያል ፤ ይህ የሚታይ አገልግሎት ይባላል ። ደዌ ሥጋውም ደዌ ነፍሱም ሲለቀውና ሲፈወስ ፤ የእግዚአብሔር ጸጋ ሲሰጠው አይታይም ፤



www.ethiopianorthodox.org

ብዙ ጊዜ ግን ከደዌ ሥጋው ሲፈወስ ይታያል ፤ ይታወቃል ፤ ኹኖም በሽታው ሲለቀው እንጂ እንዴት እንደ ዳነ ራሱ ቅሉ አያውቀውም ።

### ፫/ የምሥጢረ ቀንዲል ጥቅም ፤

በምሥጢረ ቀንዲል የሥጋንና የነፍስን ድኅነት ፤ የኀጢአትን ስርየት ፤ የነፍስን መጽናናት እናገኛለን ። ምሥጢረ ቀንዲል ከጥምቀት በኋላ ለተሠራው ኀጢአት ማስተስረያ ሲሆን ከምሥጢረ ጥምቀትና ከምሥጢረ ንስሐ ጋር ኀጢአት በማስተስረይ ድኅነትን በመስጠት ፥ ጸጋን በማስገኘት ይተባበራል ።

## ክፍል ፫ ስብከት

ሁል ጊዜ ከቅዱስ ቍርባን የማይለየው ስብከት በካህኑ መነገር መሰበክም አለበት ፤ ይኸም ተግባር የማነጽ ተግባር በመሆኑ ምእመናኑን ለቅዳሴው ለቍርባኑ እንዲዘጋጁ ያደርጋቸዋልና ።

ምሥጢረ ቍርባን እንዲሁ ያለ ምክንያት አይፈጸምም ፤ በዓል ሁኖ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ኑሮት ቅዱስ ቍርባን የተፈጸመ እንደሆነ ስብከቱ ከቅዳሴው አንደኛው ክፍል ስለሆነ በምንም መልክ መቋረጥ የለበትም ። የቀደሰው ካህን ወይም ረዳቱ የሆነው ማስተማር አለበት ፤ የጠባቂነቱን ኃላፊነት የሚወጣው በዚሁ በስብከት ሥራው ነውና ።

በስብከት ምእመናኑ በየጊዜው ይታነጻሉ ፤ ለምሥጢረ ቍርባን በቂ ሁነው ይቀርባሉ ፤ እንዲሁም በምሥጢረ ቍርባን አማካይነት ምእመናን ድኅነተ ነፍስን ያገኛሉ ፤ በዚህን ጊዜ ካህኑ ከሸክሙ አንደኛውና ሁለተኛው ቀለለለት ማለት ነው ።

ስብከት ለአመኑት ማጽናኛ መጠበቂያ ነው ፤ እንዲሁም ላላመኑት ደግሞ መሳቢያ ማቅረቢያ ጥሪ ነው ፤ ስለዚህ ስብከት በሁለት ዓይነት ይከፈላል ፤

ይኸውም ፥—፩/ የውስጥ ስብከት ፤ ፪. የውጭ ስብከት በማለት ነው።

፩. የውስጥ ስብከት ፥ በእምነት በትምህርት አንድ ሁነው በአንድ ጠባቂ ለሚመሩት ምእመናን የሚሰጠው ትምህርት የውስጥ ስብከት ይባላል ፤ ትምህርቱ እነርሱን ለማነጻት ፤ ለማጽናናት የሚሰጥ ይሆናልና ።

፪. የውጭ ስብከት ፤ ይኸም ከእምነት ውጭ ሁነው የሚገኙትን ሕዝቦች መጥራት ለክርስቲያናዊ እምነት ጥሪ የሚደረገው ነው ።



ይኸም ሁለት ዓይነት ትምህርት በአንድ አገር ውስጥም በሌላ በተለያየ አገርም ሊሆን ይችላል ።

በዚህ መልክ ካህኑ በሁለቱም ወገን የተለያየ ትምህርት በመስጠት ሁለቱንም ወገን እጅ ሊያደርግ ይችላል ፤ ይኸውም በተለያየ ቦታ በተለያየም አጋጣሚ እየተገኘ ያስተማረ እንደሆ ነው ።

ሁሉንም በአንድ ላይ አድርጊ አስተምራለሁ ያለ እንደሆነ «ዘኀሠሠ ፪ኤ ኢይረክብ ፩ደ» እንደተባለው ሁሉንም ያጣል ፤ ግን በተለያዩ ቦታዎች አጋጣሚዎች ሁሉንም በየቦታቸው ያስተማረ እንደሆነ ሁሉንም ሊያተርፍ ፥ ሁሉንም ሊያገኝ ይችላል ።

ቤተ ክርስቲያን ከመቋቋሙ ፤ ጸሎተ ቅዳሴውም ከመጀመሩ በፊት ስብከት ያስፈልጋል ፤ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያኑን የሚሠራው ማነው? አስቀድሞ ምእመናንን ማነጽ፤የምሥጢራቱም ሁሉ ተካፋይ እንዲሆኑ ለማቅረብ አስቀድሞ በቂ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋልና ። ያልዘራላት ለማብዛት፤የቅዱሳት ምሥጢራት ተሳታፊዎችንም ለማግኘት በየፅለቱ በየጊዜው ሰፊ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል ። አያጭድም፤እንዲሁም ምእመናንን ለማትረፍ ፥ የቤተ ክርስቲያንን አባ

አንድ ገበሬ ወቅቱን ጠብቆ እንዲዘራ ፥ ተግቶና ነቅቶ አዝመራውን እንዲከባከብ የምእመናኑ ጠባቂ አበ ነፍስ ነቅቶ ተግቶ ማስተማር ተቀዳሚ ተግባሩ ይሆናል ።

ካህኑ የሰው ሁሉ ጠባቂ እንደመሆኑ ሕፃናትን ፥ ጉልማሳዎችን ፥ ሽማግሌዎችን ፥ በጾታም በኩል ወንዶችን ሴቶችን ሁሉንም በትክክል ለመጠበቅ ይችል ዘንድ ሁል ጊዜ መስበክ አለበት ። ስብከቱም ሁሉንም የሚመለከት አጠቃሎም የሚይዝ መሆን አለበት ፤ ይኸም ማለት ፥

፩ኛ/ የዕድሜን ደረጃ እየለዩ ከላይ እንደገለጥነው ማስተማር ፥
፪ኛ/ የጾታውንም ሁኔታ ለይተው የሚያስተምሩበትን ጊዜ ማወቅ፥
፫ኛ/ የዕውቀት ደረጃውን ለይቶ ዐውቆ ተመጣጣኝ የሆነ ትምህርት ማስተማር ፥

ይኸም ሁናቴ በየአጥቢያው ጊዜንና ቦታን ለይቶ የሚሠራበት መሆን አለበት ፤

ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ የሆነ እንደሆነ ግን ሁሉንም እንዲያገኝ ለሁሉም እንዲያዳርስ አማካይ የሆነ ትምህርት መስጠት አለበት ፤ ያለ



www.ethiopianorthodox.org

ዚያ ሁሉም አፍረው ሊመለሱ ይችላሉ ፤ በዚህም ጊዜ ካህኑ ከዓላማው ውጭ ሆነ ማለት ነው ። ለእያንዳንዱ ምእመን የተለየ ጉብኝትና ጥበቃ ካህኑ ካደረገ የነዚህን ወገኖች ኑሮ ዕውቀት በጠቅላላም ሁኔታ ሊያውቅ ይችላል ። ካህኑ የሁሉም አባት እንደመሆኑ ሁሉም አቅንተው የሚመለከቱ ወደ እርሱ ነውና ፤ ርእሱ አእምሮውን አዘንብሎ ወደ እነርሱ መመልከት፤ ጩኸታቸውንም ማዳመጥ አለበት ። «ዘቦ ዕዝን ሰሚዓ ለይስማዕ» የሚያሰኘው እንደ ዕድሜው እንደ ዕውቀቱ እንደ ኑሮው ደረጃ ተስማሚ የሚሆነውን ትምህርት ከሰጡ በኋላ ነው ።

በጠቅላላ ስብከቱ ሰውን የሚያንጽ ሰውን የሚስብ ፣ ክርስቲያናዊ እምነትን የሚያጸና እንዲሆን ትልቅ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ። የንግግር ፈሊጥ የስብከት ዘዴ ስለሚያስፈልግ ይኸን በስብከት አቅድ የተሰጠውን ትምህርት መከታተል ያስፈልጋል ።

ምእመናኑን በስብከት ሥራ የማይገበኝ ካህን ኃላፊነቱን የዘነጋ ከጠባቂነት ሥራው ውጭ የሆነ ነው ። ከቅዳሴው ክፍል አንደኛው አካል ስለሆነ ቅዳሴው መታጎል እንደ ሌለበት ሁሉ ስብከቱም ከቶ መታጎል የለበትም ።

አንድ ካህን ምእመናንን በትክክል የሚያገኛቸው በስብከት ሥራው ነው ። «የሹም ሰነፍ ፤ ባይለፈልፍ» እንደተባለው የካህንም ስንፍና ሳይሰበክ ፤ ሳይናገር ቢቀር ነውና፤ ከፍ አድርጎ ጩኾ አሰምቶ መስበክ አለበት ።

## ክፍል ፬ ለሕሙማንና ለሙታን የሚደረግ አገልግሎት

ሀ/ በሽተኛው ምሕረትን ከእግዚአብሔር የሚያገኝበትን ጸሎት ካህኑ በየጊዜው መጸለይ አለበት ። የካህኑ ጸሎት ድውዩን ይፈውሳል፤ ኃጢአተኛውን ያነጻልና ( ያዕቆ ፭ ፡ ፲፭) ። ካህኑ አምኖ የሃይማኖት ጸሎት ስለበሽተኛው ሲጸልይ በሽተኛው እግዚአብሔር ይቅርባይ እንደሆነ ምሕረትና ጸጋ ሁሉ ከእርሱ የሚገኝ መሆኑን አምኖ ከተቀበለ ድኅነተ ሥጋን ድኅነተ ነፍስን ያገኛል ፤ ክርስቶስም ሐዋርያትን ሲልክ ከአዘዛቸው ትእዛዛት ውስጥ አጋንንትን እንዲያስወጡ ፣ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጥቶ ነው (ማቴ ፲ ፡ ፩) ።

ቤተ ክርስቲያናችን ስለድውያን የሚደረግ ምልጃ ፣ ስእለት ፤ አስተብቍዖት አዘጋጅታለች፤ይኸን በየጊዜውና በየቦታው ካህኑ በትጋት መፈጸም በግድ አለበት ።



በሽተኛውም ሳይሰቀቅ በትዕግሥት ሕመሙን መከራውንም እንዲቀበል ማጽናናት ማረጋጋት የካህኑ ዋና ተግባር ነው ። የጻድቁን የኢዮብን መከራና ትዕግሥት ምሳሌ እያደረገ ማስረዳት ማጽናናት አለበት (ኢዮ ፩፡ ፲፫ — ፲፱) ።

በሽታ በኃጢአትም ምክንያት ይመጣል ፤ ጻድቁም በሰይጣን ፈታኝነት ሊታመም ይችላል። እንዲሁ በአጋጣሚ የተለያየ ፈተና የሚገጥመው ሰው ይገኛል ፤ ስለዚህ ሁሉ በትዕግሥት የፈጣሪያቸውን ይቅርታ ደጅ እንዲጠኑ እንጂ እንዳይመረሩ ተስፋም እንዳይቈርጡ ካህኑ ነቅቶ ተግቶ ማጽናናት ማረጋጋት አለበት ። ካህኑ የእግዚአብሔር እንደራሴ እንደመሆኑ በሥቃይ የተያዘው ሰው ካህኑን ሲመለከት በተስፋ ይጽናናል ፤ ይፈወሳልም ፤ ስለዚህ ካህኑ በጧትም በማታም ይኸን ተግባር አድርጎ መያዝና መፈጸም አለበት ። ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ድኅነት ከቶ ሊገኝ አይችልም ፤ ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህኑ ከምእመኑ መለየት የለበትም ።

ለ/ ሙታን ፣ ሙታንም የእግዚአብሔር ወገኖች ናቸው ፤ እግዚአብሔር አምላክ የሙታንም የሕያዋንም አምላክ ነውና ፤ ሕያዋንንም ሙታንንም ይገዛልና (ጸሎተ ሃይ ፡ ፩) ።

ሙታን ወደ እግዚአብሔር ቀረቡ እንጂ አልራቁም ፤ ዐረፉ እንጂ አልሞቱም ፤ ስለዚህ ወደ መቃብር በድናቸው ከመውረዱ በፊት ልዩ ክብር ይሰጣቸዋል ፤ የተለየ ጸሎትም ይደረግላቸዋል ፤ እንደቤተ ክርስቲያን በዓል ሁኖ የምእመኑ አማኝነት ሠራተኛነት ፣ ተጋዳይነት እየተነገረለት ፤ እንደአቸናፊነቱ እንደ ድል አድራጊነቱ የአበባ ጉንጉን ተደርጎለት በክብር ይሸኛልና ።

ቤተ ክርስቲያናችን ስለዚህ ፍትሐተ ጸሎት ፣ ወይም ጸሎተ ሙታን ብላ የወሰነችው ስላላት በትክክል መፈጸም አለበት ፤ ካህኑ ይኸን የፈጸመ እንደሆነ የጠባቂነቱን ኃላፊነት ተወጣ ፤ እውነተኛ የእግዚአብሔር ካህንነቱን ገለጠ ማለት ነው ።

## ክፍል ፭ የቤተ ክርስቲያን ዶግማ

ካህኑ ደህና አድርጎ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውን የራሱን ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት (ዶግማ) ማወቅ ለሌላውም ማሳወቅ አለበት ።



www.ethiopianorthodox.org

የቤተ ክርስቲያን ዶግማ በአጠቃላይ በ፮ ክፍል ይከፈላል ፤ ይኸውም

፩/ የእግዚአብሔርን ህልውና ማወቅና ማመን ፣ ይኸም ማለት እግዚአብሔር አምላክ የነበረ ያለ ፣ የሚኖር አምላክ እንደሆነ ሁሉ በእርሱ የሆነ ያለ እርሱ አንድም የሆነ የሌለ አምላክ እንደሆነ ማመንና ማሳመን ነው ፤ይኸም እምነት በቅ/ መጽሐፍ እየተደገፈና በሥነ ፍጥረት አማካይነት የተረዳ እውነተኛ እምነት መሆኑን ማወቅና ማሳወቅ አለበት ። (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳፩) ።

፪/ እግዚአብሔር በሦስትነት፤እግዚአብሔር በአንድነቱ በሦስትነቱ ጸንቶ ያለ አምላክ ስለሆነ ሦስትነቱ በአንድነቱ ሳይጠፋ በሦስትነቱም ርባኤን ሳያመጣ የሚኖር አምላክ መሆኑን ጠንቅቆ ማወቅና ማመን ሌላውንም በዚሁ ማሳመን የካህኑ ተግባር ነው ።

፫/ ዓለም በጠቅላላ ፤ ሰማይና ምድር በውስጣቸው የሚገኙ ሁሉ የሚታየውም የማይታየውም የራቀውም የቀረበውም ሁሉ በእግዚአብሔር ፈጣሪነት እንደተፈጠረ ማመንና ማሳመን ፣ ይኸም ለተቀደሰ ዓላማ እንጂ በከንቱ ለከንቱ ያልተፈጠረ መሆኑን ካህኑ ደኅና አድርጎ ማወቅ ማመን ሌላውንም ማሳመን አለበት ።

፬/ ድኅነተ ዓለም ፤ ዓለም ከተፈጠረ በኋላ በሰው በደል ምክንያት ለጥፋት ተዳርጎ መኖሩ የታወቀ ነው ፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ምሕረቱ ብዙ ነውና ስለታረቀው ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንድያ ልጁን እንደላከ ፣ ግልጥ የሆነ ክርስቲያናዊ ትምህርት ነው ። የእግዚአብሔር ፍጹም ፍቅር የተገለጠው በዚህ ዓለም ድኅነት ነው። የዘለዓለም ተስፋቸው ከዚሁ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ካህኑ ይኸን ማወቅና ማሳወቅ አለበት ።

፭/ ምሥጢረ ተዋሕዶ ፤ ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ ስለሆነ አምላክ ወሰብእነቱ በተዋሕዶ መሆኑን ማመን ተገቢ ነው ፤ ይኸውም መለኮት ከሥጋ አካልና ከሥጋ ባሕርይ ጋር ፣ ሥጋም ከመለኮት አካልና ባሕርይ ጋር ተዋሕዶ አምላክ ወሰብእ መባሉ ረቂቅ ምሥጢር እውነተኛም ሃይማኖት መሆኑን ፣ ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ምክንያት የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እየተባለች የምትጠራ መሆኗን ካህኑ መረዳትና ማስረዳት አለበት ፣ ይኸንንም ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ሃይማኖት ካህኑ መጠበቅ ማስጠበቅም ግዴታው ነው ።

፮/ ምሥጢረ ምጽአት ፣ ክርስቶስ ለሁለተኛ ጊዜ ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ፣ይኸንም ዓለም አሳልፎ ሌላ አዲስ ዓለም እንደሚተካ ኦርቶዶክሳዊ እምነታችን ነው ። ስለዚህ ካህኑ ይኸን የመጨረሻ የማጠቃለያ እምነት ከፍተኛ ግምት ሰጥቶ ሊጠብቀው ሊያስጠብቀው ይገባዋል።

ከተናገርናቸው አምስቱ የዶክትሪን ትምህርቶች የተገለጡና የተፈጸሙ ናቸው ፤ የመጨረሻው ስድስተኛው ትምህርት ግን ገና በተስፋ የምንጠብቀው ስለሆነ ካህኑ በሚያጓጓ ምእመናን እንዲጠብቁ ተስፋም አድርገው ደጅ እንዲጠኑ ማስተማር አለበት ።

በዚህ ዓለም ሳለን ስለሠራነው ሁሉ ምስጋና የምናገኝበት ፤ ዋጋ የምንከፈልበት በሁለተኛ ጊዜ መምጣቱ ስለሆነ ይኸን አምኖ ተስፋም አድርጎ መጠበቅ ተገቢ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ማኅበረ ቅዱሳን ... ቤተ መጻሕፍት

# የካህናት ተልእኮ

## ማውጫ

ገጽ


መቅድም ፡ . . . . . . . ፶፩

## ክፍል ፩ እውነተኛው ካህን

፩/ የክህነት ትርጉም ፶፯
፪/ የክህነት አጀማመር ፶፰
፫/ የብሉይ ኪዳን ካህን ፶፱
፬/ የሐዲስ ኪዳን ካህን ፷፩
፭/ ለክህነት አገልግሎት መጠራት ፷፫
፮/ ክህነት ቅዱስ አገልግሎት መሆኑ ፷፮
፯/ የካህኑ መለያ ምልክት ፷፯

## ክፍል ፪ ሥርዐተ አምልኮ

፩/ ሥርዓተ አምልኮን መፈጸም ፸፮
ሀ/ ለጸሎት ጽሙድ መሆን
ለ/ ጸሎተ ቅዳሴን በየጊዜው መፈጸም
ሐ/ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸም ፸፰

## ክፍል ፫ የማያቋርጥ ስብከት መስበክ ፻

ሀ/ የዕድሜን ደረጃ በመለየት መስበክ
ለ/ ልዩ ልዩ አጋጣሚዎችን በመጠበቅ መስበክ

## ክፍል ፬ ለሕሙማንና ለሙታን የሚደረግ አገልግሎት ፻፪

## ክፍል ፭ ትምህርተ ሃይማኖትን ማስተማር ፻፫


www.ethiopianorthodox.org